ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና

የክዋኔ ኦዲት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው 1146/2011) አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15፤ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ በኢንቬስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስግ እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) ፤ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርት፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፣ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች

ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውንና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በኢንቬስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስ (Investment Project Financing) እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) ተከታታይ እና ማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ሂሳብ በተመለከተ የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርት፤

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ እና በመንግስትና በልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ ፕሮግራሞችን ኦዲት፤

3. የ2012/13 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የተከናወኑ ልዩ ኦዲት ስራዎች፤ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን በአጭሩ ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2012 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች፣ በፋይናንስና ሕጋዊነት የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 8 መ/ቤቶች ፤የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 41 መ/ቤቶች፣ እንዲሁም የ17 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲት እና 3 የክትትል ኦዲት ሪፖርቶች ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ 2 ጥራዞች/የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ

ኦዲት ሪፖርት እና አጠቃላይ ዘገባ/ እና ሌሎች የተጠቀሱት ሪፖርቶች በሶፍት ኮፒ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. በዚህ ሪፖርት ውስጥ ተካተው ለተከበረው ም/ቤት የቀረቡት የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም በላይ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የመንግሥት የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

7. የ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ መሠረት ያደረገው የመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 (1146/2011 እንደተሻሻለው) አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1-15 እና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001(970/2008 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀፅ 2 ነው፡፡ በየዓመቱ በየካቲት ወር በማቀድ፤ የኦዲት ሥራውን በመጋቢት ወር የመጀመር በቀጣዩ በጀት ዓመት ጥር 30 ላይ ለማጠናቀቅ ቀደም ሲል ልማድ በመኖሩ፤ በ2012/13 ኦዲት ዓመት በዚሁ ለመቀጠል በመጋቢት/2012 መጀመሪያ ላይ ቢታቀድም፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ዕቅዱንና የስራ መጠናቀቅያ ጊዜያችንን ለመከለስ ተገደናል፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 189 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች 179 መ/ቤቶችና 50 ቅ/ጽ/ቤቶችን በመ/ቤታችን ኦዲት ለማድረግ፤ 10(አስር) በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኦዲት በማስደረግ ተደርሶበት የነበረውን የኦዲት ሽፋን 100% ለማስቀጠል በመጋቢት /2012 ታቀዶ የነበረ ቢሆንም፤ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት ከ5 ወራት በላይ ኦዲተሮቻችንና የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችም በስራ ላይ ስላልነበሩ፤ ከፍተኛ በጀት ለሚያንቀሳቅሱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ትኩረት በመስጠት የ117 መ/ቤቶችና 36 ቅ/ጽ/ቤቶች የሕጋዊነት ኦዲት ለማድረግ ከመስከረም 25/2013 ጀምሮ እስከ የካቲት 30/2013 ለማጠናቀቅ ዕቅዱ ተከልሷል፡፡

9. በተከለሰው ዕቅድ መሰረትም የ117 መ/ቤቶችና 35 ቅ/ጽ/ቤቶች የህጋዊነት ኦዲቶች ስለተጠናቀቁ የዕቅድ ክንውኑ 99.15% ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ ከነዚህ ውስጥ የኦዲት ስራቸው ተጠናቆ በተለያዩ ምክንያት ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር የመውጫ ስብሰባ ለማድረግ ያልተቻለና ለተላከው የስራ አመራር ሪፖርት ምላሽ ያልሰጡ የ12 መ/ቤቶች ግኝቶቹን በዚህ ሪፖርት ውስጥ ለማካተት አልተቻለም፡፡

<u>የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች</u>

<u>የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች</u>

10. የ2012 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ117 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የሥራ አመራርና የኦዲት ሪፖርቶችን ተዘጋጅተው ለየመ/ቤቶቹ የተላኩ ሲሆን፣ የባለበጀት መ/ቤቶቹ ሪፖርቶችም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2010 እና 2011 ካሉት በጀት ዓመታት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት አስተያየቶች ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ብዛት		
	2010	2011	2012
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	25	29	10
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	89	71	46
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	11	5	8
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	49	48	41
የኦዲት ስራው የተቋረጠ	1	1	
ሒሳባቸው ባለመዘጋቱ የሥራ አመራር ሪፖርት ብቻ የተላከና የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት	1	1	
ለስራ አመራር ሪፖርት ምላሽ ቢሰጡም የመውጫ ስብሰባ ባለመደረጉ በዚህ ዘገባ ውስጥ ያልተካተቱ		15	12
ድምር	**176**	**170**	**117**

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

11. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ለ2012 በጀት ዓመት ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከህግና ከተዘረጋው አሠራር ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፣ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ የሚገቡ አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

12. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 67,856.61 እና የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብር 9,536.18 በድምሩ ብር 77,392.79 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

13. በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በገቢዎች ሚ/ር አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቆጠራው ከመዝገብ ጋር ሲነፃፀር በብር 76,723.77 በማነስ የታየ ሲሆን፣ በ2 መ/ቤቶች ብር1,436,404.83 የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ/ዴቢት/ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ባለበጀት መ/ቤቶች ያልተጠቀሙበት ጥሬ ገንዘብና በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ ሊያደርጉ የሚገባ ቢሆንም፣ በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 39,178,285.72 ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ፣ እንዲሁም በ6 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

14. የተዘረጋውን ሥርዓት ተክትሎ በጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት፣ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ፣ በማነስ የታየውም ልዩነት ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና የታዩት የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ፣ እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳየውም የተጣራ ሀብት ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

<u>የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ</u>

15. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ90 መ/ቤቶች እና በ12 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 7,480,256,624.50 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ ብር 106,795,353.90 መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

16. በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፣ የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,943,001,905.94፣ የጤና ሚኒስቴር ብር 1,557,855,784.51፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 614,701,418.01፣ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 402,816,388.00፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 385,208,574.64 እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

ብር 336,693,891.08፣ የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 290,773,382.92፣ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 174,068,511.51፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 126,633,284.49 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

17. በወቅቱ ያልተወራረደው ተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፣ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 1,856,664,039.36፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 2,463,789,581.69፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 1,026,760,295.15 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 257,670,576.72 ሲሆን፣ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,875,372,131.58 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡

18. ከላይ በፓራግራፍ 15 ከተጠቀሰው ተሰብሳቢ ሂሳብ በተጨማሪ በ9 መ/ቤቶችና በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 68,388,729.52 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲሆን፣ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 30,754,257.50፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,064,097.42 እና የገቢዎች ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት ብር 12,775,778.05 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡ በየመ/ቤቱ እየታዩ ያሉት ተሰብሳቢ ሂሳቦች እያጨመረ መሄዱና በወቅቱ አለመወራረድ በቆይታ ብዛት ገንዘቡን ያለመሰብሰብ ዕድሉን ያሰፋዋል፡፡

19. በመሆኑም መ/ቤቶች ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቦቹን ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተከታትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ተጣርቶ ትክክለኛነቱ በማስረጃ እንዲረጋገጥና እንዲሰበሰብ ወይም እንዲወራረድ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የገቢ ሂሣብ

20. የመንግሥት ገቢ በወጡት ሕጎች መሠረት በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ

21. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መ/ቤቶች እና በስራቸው ባሉ 12 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የንግድ ትርፍ ግብር፤ የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ብር 353,628,975.23 እና በሌሎች በ31 መ/ቤቶችና 1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 36,397,899.14 በድምሩ ብር 390,026,874.37 የገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ተገኝቷል፡፡

22. በደንቡ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል በገቢዎች ሚኒስቴር የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 171,150,671.02፣ ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 38,870,163.19፤ ምስራቅ አ.አ/አ/ግ/ከፋዮች ብር 29,265,133.90 እና የጉምሩክ ኮሚሽን የድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 79,820,647.22 እና ሞጆ ቅ/ጽቤት ብር 8,222,706.01 ከፍተኛው ሲሆኑ፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,071,757.37 እና የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 2,471,381.76 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

23. በመሆኑም መ/ቤቶቹ ለወደፊቱ የመንግሥትን ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣና ውል ማስከበሪያ ሂሳብ

24. በፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሠረት አቅራቢው ሣይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግሥት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10% ሣይበልጥ የጉዳት ካሣ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሠረት መ/ቤቶች በውሉ መሠረት ባልፈጸሙት አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ላይ በመመሪያው

መሠረት ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑ ሲጣራ 14 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 70,329,574.42 የጉዳት ካሣና ውል ማስከበሪያ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ የጉዳት ካሣና ውል ማስከበሪያውን ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤- የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ብር 30,619,666.68፤ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,595,365.30 እና አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,780,968.79 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

25. በተጨማሪም መንግስት ወጪያቸውን ሸፍኖላቸው የተማሩ ሰራተኞች፤ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው መሰብሰብ የነበረበት የትምህርት ክፍያ በ4 መ/ቤቶች ብር 31,064,249.40 ገቢ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

26. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በመንግሥት መመሪያና በገቡት ውል መሠረት እስከ አሁን ያልተሰበሰበውን የጉዳት ካሣና ሌሎች ገቢዎች እንዲሰበስቡና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሠረት እንዲፈጽሙ አሳስበናል፡፡

<u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ</u>

27. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎች ሚኒስቴር ስር ባሉት በ6 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር ባሉት 6 ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ኦዲት/በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ውሳኔ መሰረት ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ ብር 7,701,064,157.75 እና በ2 መ/ቤቶች ከውዝፍ ያልተሰበሰበ ብር 70,487,155.65 በድምሩ ብር 7,771,551,313.40 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

28. ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎች ሚኒስቴር ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,774,145,453.52 ፣ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 678,568,502.57፣ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,486,900,067.59፣ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,020,938,142.61፤ የምስራቅ አዲስ አበባ አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 398,863,093.67 እና ሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 233,369,525.84 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

29. በተጨማሪም ከውዝፍ ገቢ ጋር በተያያዘ በቫውቸር ሥርዓት ከቀረጥ ነጻ ገብተው በጊዜ ገደቡ ምርት ላይ ስለመዋሉና ምርቱም ለውጭ ገበያ የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበለት ያልተሰበሰበ የቀረጥና ታክስ በ2 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 262,724,586.86፣ ዋስትና በማስያዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች የሚቆዩበት ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም የተያዘው ዋስትና ሂሳብ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ወይም ዋስትናው ያልተራዘመ የቀረጥና ታክስ በ3 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 266,572,006.53 በወቅቱ ያልተሰበሰበ እና በግብር ከፋዮች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ዕዳ አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ግብር በ1 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 13,800,542.68፣ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

30. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት የሚያከናውናቸውን ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና መሠረተ ልማት ለመዘርጋት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶና ከመረጃ አለመጥራትና አለመናባብ ጭምር ያሉት ክፍተቶች ተፈትተው የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ</u>

31. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ7 መ/ቤቶች ብር 167,525,833.56 የገቢ ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ ተገኝቷል፡፡

32. የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አሁንም አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፣ ይህ አሰራር በገቢ ሂሳብ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ለምዝበራ በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ፣ መ/ቤቶቹ የሚያዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎችና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

33. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውንም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ እንዲመዘግቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸው በማካተት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያደርጉ፣ እንዲጠቀሙበት በሕግ ያልተፈቀደለቸውን ገቢ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

34. የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 42,979,950.91 እና በ5 መ/ቤቶች ከኪራይ እና ከተለያዩ የገቢ ማመንጫ የተሰበሰበው ገቢ ብር 49,010,702.44 አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

35. በሌላም በኩል በናሙና ከታዩት ፋይሎች በ2 የገቢዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤቶች ቫት/ቲኦቲ ያላስታወቁ ብዛት 68፤ የንግድ ትርፍ ያላስታወቁ 39 ግብር ከፋዮች እና ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ያላስታወቀ 1 በድምሩ 108 ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ያላሳወቁ በመሆኑ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነና ስለመክፈላቸው ወይም ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

36. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች ዝርዝር በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ግብር ከፋዮች የሚፈለግባቸውን ግብር በሙሉ በወቅቱ አሳውቀው እንዲከፍሉ ተገቢውና ጥብቅ ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሣብ

37. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም በግዢ አዋጅና መመሪያ መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውና መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡንና ሪፖርት መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

38. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 475,011,010.41 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

39. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር 230,601,274.84፣የኢሚግሬሽን ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ብር179,851,030.67፤ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 38,499,005.99፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 5,856,698.11፤ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርስቲ ብር 2,986,562.22 እና አሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 2,906,485.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

40. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያዎች እንዲሁም በግዢ አዋጁና መመሪያው መሠረት ወጪውን የሚደግፉ ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

<u>ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

41. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ62 መ/ቤቶችና በ11 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 96,887,412.07 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

42. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 16,519,042.26፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 10,401,053.00፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,901,224.58፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 7,474,758.69፤ እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ 7,097,200.00፤ የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,396,358.57 እና ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 4,925,882.50 ናቸው፡፡

43. በተጨማሪም በ10 መ/ቤቶች እና በ1ቅ/ጽ/ቤት በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ ብር 277,744.90፤ በ9 መ/ቤቶች በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ ብር 48,763,691.14፤ በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ በ2 መ/ቤቶች ለሶስተኛ ወገን የተሰጡ የጥበቃና ፅዳት አገልግሎት ብር 31,277,757.32 እና በ7 መ/ቤቶች ብር 4,277,091.64 የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቶል፡፡

44. እንዲሁም በ7 መ/ቤቶች ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 10,566,408.58 የተፈጸሙ ክፍያዎች እና በ6 መ/ቤቶች የግብር መቀጫ፣

የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመክፍሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት፣ የተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ቦሎ ምርመራ በወቅቱ ባለመደረጉ፣ እቃው ሳይነሳ ለዘገየበት ለመጋዘን ኪራይ ተጨማሪ ክፍያ እና የተሰበሰበውን የቅድሚያ ገቢ ግብር በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ ባለመደረጉ ምክንያት ተጨማሪ ክፍያና የቅጣት ብር 9,679,382.20 ክፍያ ከመንግስት ካዝና ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

45. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ክፍያውን ካፀደቁትና ከፈፀሙት ላይ ተመላሽ እንዲሆን፣ የክፍያ ስርዓት ለሌላቸው ሥርዓቱን በመዘርጋትና በማስፈቀድ ለወደፊቱ ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

<u>**በብልጫ የተከፈለ ወጪ**</u>

46. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ የተከናወኑ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፤ በ39 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 2,968,242.92 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 31,799,303.54 በጠቅላላው ብር 34,767,546.46 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በአራት መ/ቤቶች ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ስምምነት ያልቀረበለትና ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በድምሩ ብር 28,718,783.60 አላአግባብ በብልጫ የፈፀመ ክፍያ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

47. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ያለበቂ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ ከተገባው ውል ውጭ በመክፈል፣ ለደመወዝ ከሚገባው በላይና ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል፤ እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት እና ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም በብልጫ የተከፈሉ ይገኙበታል፡፡

48. ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ ከህግ ውጪ ከመሆኑም በላይ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግና ለሙስናም በር የሚከፍት አሠራር ነው፡፡ በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ህግጋት፤ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ

እንዲሆንና አስፈላጊውም አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የግዥ አዋጅና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች

49. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት የግዢ አዋጅና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ60 መ/ቤቶችና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 98,897,086.74፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 13,194,299.94፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 318,467,340.17፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 1,631,871.02 የጨረታ ሰነድ ያልቀረበለት ብር 743,293,348.56 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 34,465,249.82 በድምሩ ብር 1,209,949,196.25 የመንግሥት የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

50. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፤ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 753,477,422.26፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 254,815,419.07፤ የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 19,885,825.92፤ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,203,118.39፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 13,293,658.00፤ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር11,610,938.73 እና አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,352,408.86 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

51. የግዥ መመሪያን ሳይከተሉ ግዥ መፈጸም የህግ ጥሰት ከመሆኑም በላይ መንግሥት ተወዳዳሪ ዋጋ እንዳያገኝ ለምዝበራና ለጥራት መጓደል የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የመንግሥት ግዥ አዋጅና መመሪያን አክብረው እንዲሰሩ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ንብረቱ ገቢ ስለመሆኑ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

52. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች በብር 4,929,470.29 ተገዙ ተብሎ ለተከፈለው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ

ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 799,090,417.48 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብ የቀረጥ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

53. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚገዛው ማንኛውም ንብረት የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶለት ለመ/ቤቱ ገቢ ተደርጎ ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግሥትና የህዝብ ንብረትና ገንዘብ በቀላሉ ለብክነትና ለሥርቆት ሊዳረግ ይችላል፡፡

54. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡ የተከፈለበት ንብረት በዕቃ ገቢ ደረሰኝ ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ ካልሆነም ከሚመለከታው አካል ጋር ተነጋግረው አሠራር እንዲዘረጋለት እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

<u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ</u>

55. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶችና 1 ቅ/ጽ/ቤት ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 37,487,550.73 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

56. የቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,290,638.97፣ አሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 10,429,925.35 እና የአዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት ብር 5,000,000.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡

57. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ የወጪ ሂሳብ

58. በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸውና ትክክለኛ ወጪ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶችና 1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 156,342,787.75 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

59. ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- ብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 104,396,275.38፤ ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር44,482,515.23፤ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር1,362,723.49 መዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,072,851.36፣ ዋና ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

60. ከዚህ በተጨማሪ በ4 መ/ቤቶች ብር 35,247,247.96 የያዙ ሰነዶች ለኦዲት ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

61. ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ የመንግሥትን ገንዘብ ወጪ ማድረግ ህግና አሠራር መጣስ ከመሆኑም በላይ የህዝብንና የመንግሥትን ገንዘብ ለጥፋትና ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ ሆኖ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፣ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

የማማከር ፈቃድ ሣይኖር ያለአግባብ ተረጋግጦ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ

62. ማንኛውም ግንባታ ሲከናወን ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ የማማከር አገልገሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ ድርጅት ሲረጋገጥ ብቻ ክፍያዎች ሊፈጸሙ ይገባል፡፡ ሆኖም የግንባታ ፕሮጀክቶችን ሥራ እንዲከታተሉ በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ እንደ አንድ የስራ ክፍል የተቋቋሙ ነገር

ግን የማማከር ፈቃድ በሌላቸው የግንባታ ጽ/ቤቶች የክፍያ ሠርቲፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በማከናወን በ2 ዩኒቨርሲቲዎች ብር 35,634,418.75 ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ አሠራር ህጋዊ ባለመሆኑ እንዲቋረጥ ከ2007 ጀምሮ ብናሳስብም የተወሰኑ ተቋማት እርምጃ ሳይወስዱ አሁንም ተግባሩን ገፍተውበታል፡፡

63. ግንባታዎች በተገቢው ጥራትና በዲዛይኑ መሠረት ስለመሠራቱ በህግ አግባብ ዕውቅና በተሰጠው ገለልተኛ አካል ማረጋገጫ ተሰጥቶ ክፍያ ካልተፈጸመ የተከናወነውን ግንባታ በተመለከተ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ስለማያስችል መ/ቤቶቹ እየተከተሉት ያለው አሠራር በፍጥነት እንዲቋረጥና ለግንባታዎች ተገቢው ዕውቅና ያለው አማካሪ ድርጅት እንዲቀጠር ቀደም ባሉት ዓመታትም በተደጋጋሚ ብናሳስብም አሠራሩን ለማረም ፈቃደኛ ያልሆኑ አሁንም በመኖራቸው በነኚህ ተቋማት ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

64. በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን እና ሂሳባቸውም በተከፋይ መያዝ የሚገባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ69 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 695,222,470.91 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ ከተጠቀሰው ተከፋይ ሂሳብ በተጨማሪ በ6 መ/ቤቶችና በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 174,125,137.87 ተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ ቢሆንም፣ ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የተከፋይ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

65. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች መካከል፣- የኢኖቬንሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 151,662,818.89፣ ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ብር 104,114,901.03፣ ብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 55,751,342.41፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,250,690.28፣ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር29,690,128.18፣ የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 28,526,788.35 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

66. የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 97,594,987.48፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 357,330,411.56፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 81,615,818.49 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 6,770,830.39 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 151,910,422.99 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡

67. በመሆኑም የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ በፋይናንስ ሕጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፈል፤ ትክክለኛነቱን ማጣራት ያልተቻለውም ተከፋይ ሂሳብ ዝርዝር ማስረጃ በጥንቃቄ ተጣርቶ ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

68. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶችና 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና በጀት ሳያዛውሩ ከመደበኛ በጀት ብር 519,294,417.83፣ የውስጥ ገቢ ብር 56,630,607.41 እና ከካፒታል በጀት ብር 270,509,795.62 በድምሩ ብር 846,434,820.86 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

69. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ከተጠቀሙ መ/ቤቶች መካከል፤ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 262,849,358.88፤ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 248,751,857.59፤ የኢሚግሬሽን ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ብር 76,162,473.85፤ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 58,762,434.17፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,915,518.77 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

70. በጀት ሳይፈቀድ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተከለከለ በመሆኑ መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተፈቀደላቸውን አሠራር በመከተል በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ ለበርካታ ዓመታት እንዲያርሙ አስተያየት የተሰጣቸው ቢሆንም ጉዳዩ እየተሻሻለ ባለመሆኑ ም/ቤቱና የገንዘብ ሚኒስቴር ተገቢውን አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የንብረት አስተዳደር

71. በየዓመቱ በምንሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሠረት በርካታ መ/ቤቶች የንብረት አስተዳደራቸውን ለማሻሻል ጥረት እያደረጉ ቢሆንም አሁንም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በገሃድ ይታያሉ፡፡ በዚህ ረገድ በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ኦዲት ሲደረግ ከንብረት አስተዳደር አንፃር የሚከተሉት ጉድለቶች ታይቷል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	15	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	9	4
ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	14	
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	6	3
የአላቂ የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	21	2
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	44	3
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	56	8
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	15	
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	10	2
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ ፤	3	

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
የንብረት ጥበቃ ላይ ተመድበው ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች	1	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸውና ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ:-/ 32 ተሽከሪካሪዎችና ሌሎች የተለያዩ ዕቃዎች /		6
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር 5,789,078.63 ይገኙበታል)	15	3
በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎች ዋጋ ያልተመኑ መሥሪያ ቤቶች፤	1	2
አገልግሎት የሚሰጡና የማሰጡ ዕቃዎች ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑ		6
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	15	1

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

72. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲመራ፤ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

73. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ጉድለቶች ታይተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	የተሽከሪካሪዎች ብዛት		
	የመ/ቤቶ ች/ቅ*	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች/**
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	13/3	85	11/6
በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆሙ	37/4	473	27/65
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	2/2	5	11
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	21/4	188	20
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	1	5	4
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት ያለው	1	8	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው/ጌጅ/ የማይሰራ	9	85	4
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	10/1	89	4
ታርጋቸው ኢ.ት ያልሆነ	3	34	61/2
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1/1	1	4

* ሌሎች- ሎቤድ፣ትራክተር፣ ባጃጅ

መኖራቸው ታውቋል፡፡

74. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ፣ ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የኢንቨስትሜንት ፕሮጀክት ፋይናንስንግና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም በተመለከተ

75. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት በየሩብ ዓመቱ የኢንቨስትሜንት ፕሮጀክት ፋይናንስንግ እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የአገልግሎቱ አቅራቢ በሆኑት በወረዳና በክልል ደረጃ በሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክተሮች እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ኦዲት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

76. በዚሁ መሰረትም ከክልሎች በናሙና በተመረጡ ወረዳዎች ፣ የፕሮገራሙ ፈጻሚ በሆኑ የከተማ አስተዳደር፣ የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የክልል ሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት 159 ፣ የማረጋገጫ ስራዎችን 27፤ ዓመታዊ ኦዲት ግብአት 9 እና የማጠቃለያ ኦዲት 1 በድምሩ 196 ኦዲቶችን ለመስራት በእቅድ ተይዞ ነበር፤ አፈጻጸሙም አንድ ልዩ ኦዲትን በመጨመር 197 ወይም 100.51% የኦዲት ስራዎችን በማከናወን ሪፖርቱም ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ተልኳል፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ

77. በገንዘብ ሚንስቴር የተዘጋጀዉ የ2011 እና የ2012 በጀት አመት የፌደራል የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ተከናዎኖ ሪፖርቱ ለሚንስቴር መ/ቤቱ እና ለተወካዮች ም/ቤት ለየተላከ ሲሆን፤ የ2012 በጀት አመት በኦዲት ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

78. ቀደም ብለው ከተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ገቢ፤በበጀት አመቱ ከተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ገቢ፤ከተሸጡ ድርጅቶች የሊዝ ክፍያ፤ ከልማት ድርጅቶችና ወደ ግል ከተዛወሩ ድርጅቶች የብድር ተመላሽ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ከ23 ድርጅቶች ሽያጭ ያልተሰበሰበ ብር 4,598,890,000.00 ተገኝቷል፡፡

79. መንግስት ከውጭ ሀገር በብድር ያገኘውን ገንዘብ በመልሶ ማበደር ስምምነት መሰረት ለልማት ድርጅቶች የሚያበድር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ተበዳሪዎች ከመንግስት የተበደሩትን ገንዘብ በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ከተለያዩ 7 ድርጅቶች ከ2001 እስከ 2012 ድረስ፡-በድምሩ ብር 14,020,071,043.29 በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

80. የመንግስት ልማት ድርጅቶች የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ገቢ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-እስከ ሰኔ 30, 2012 በጀት ዓ.ም ድረስ ከተለያዩ 11(አስራ አንድ) ድርጅቶች፡በድምሩ ብር 6,993,600,000.00 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

<u>የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ</u>

81. መ/ቤታችን ከፋይናንስና የሕጋዊነት (Regularity) ኦዲት በተጨማሪ በክዋኔ ኦዲት ላይ ትኩረት ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፤ እንዲሁም ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ በመጋቢት 2012 ተጀምረው እስከ ጥር 30/2013 የሚጠናቀቁ 24 የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን ታቅዶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት የኦዲት ሥራውን በዕቅዱ መሠረት በመጋቢት ወር 2012 መጀመር ባለመቻሉ የ2012/13 የኦዲት ሥራው በተጨባጭ የተጀመረው በመስከረም ወር 2013 የመጨረሻው ሳምንት በመሆኑ፤ ዕቅዱም ተከልሦ 23 አዳዲስና 4 የክትትል ኦዲቶችን ብቻ በድምሩ 27 ኦዲቶችን ለማከናወን ታቅዷል፡፡

82. በዚህም መሠረት የ17 አዳዲስ ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በታቀደው መሠረት ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን፣ 5ቱ ክዋኔ ኦዲቶች ሥራቸው ተጠናቅቆ ከፊሎቹ የኦዲት ተደራጊውን ምላሽ ከፊሎቹ ደግሞ የመውጫ ስብሰባ የሚጠባበቁ ናቸው፡፡ ቀሪው አንድ ሥራ ተጀምሮ ሣይጠናቀቅ ወደ 2013/14 የኦዲት ዘመን ተሸጋግሯል፡፡ የክትትል ኦዲቶችን በተመለከተ የ3 ክትትል ኦዲቶች ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቶቹ ወጪ ሆኗል፡፡ በዚህም መሠረት የዓመቱ የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም 74.00% ሲሆን፣ ሌሎች ተግባራት ተጠናቅቀው የመወጫ ስብሰባና የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ የሚጠባበቁት ሲጨመሩ ክንውኑ 92.59% ይሆናል፡፡

83. የኦዲት ሪፖርታቸው ወጪ የሆኑት የ17ቱ አዳዲስና የ3ቱ የክትትል ኦዲት ሪፖርቶች ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመስኖ ልማት ኮሚሽን የላይኛው ጉደር ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ዝግጅትና አፈፃፀም

84. ኮሚሽኑ ለሥራው እንዲለቀቅለት የሚፈለገውን መሬት መጠንና የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ ውሳኔ የተሰጠበት ማስረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ማቅረብ ያለበት ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ለከተማው ወይም ለወረዳዎች ይህንን መረጃ ሣያሳውቅ፣ ስራ ተቋራጭ ድርጅቶች ወደ ስራ ከገቡ በኋላ እንዲለቀቅ የሚፈልገውን መሬት ከባለ ይዞታዎች ነፃ እንዲሆን አማካሪ ድርጅቱ የካቲት 4 ቀን 2012 (እ.ኤ.አ.12/02/2020) በቁጥር WED172/94/20 በፃፈው ደብዳቤ ኮሚሽኑን ከጠየቀ በኋላ ኮሚሽኑ የካቲት 12 ቀን 2012 በቁጥር መልኮ01/19/286 ለቶኬ ኩታዬ ወረዳ እንዲሁም የካቲት 19 ቀን 2012 በቁጥር መልኮ 02/19/298 ለድሬ እንጭኒ ወረዳ አስተዳደር በተፃፉ ደብዳቤዎች የካሳ ግምት ተሰርቶ እንዲላክለት ዘግይቶ በመጠየቁ በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ ችግር የሚያስከትልና የካሳ ክፍያውም ግልፅነት እንዳይኖራውና ለመንግሥትና ህዝብ ገንዘብ መመዝበር ምክንያት ሊሆን የሚችል መሆኑ፣

85. የላይኛው ጉደር የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ከአማካሪ ጋር ውል ከተፈራረመ በ15 ቀናት እና የስራ ተቋራጮች ውል ከተፈራረሙ በ30 ቀናት በኋላ ስራ ሊጀምሩ የሚገባ ቢሆንም፤ የመስኖ ውሃ የሚሄድበት መስመር ዝርጋታን /Irrigation and Drainage system/ ከሚያከናውነው የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ጋር ኮሚሽኑ ውል የተፈራረመው ሰኔ 17 ቀን 2011 ዓ.ም. (June 24, 2019) ቢሆንም የግንባታ ስራ የተጀመረው አንድ አመት ከአምስት ወር ከዘገየ በኋላ ታህሳስ 6 ቀን 2013 ዓ.ም. (December 15, 2020) ሲሆን፤ የግንባታ ስራው በአሁኑ ወቅት 50% መድረስ የነበረበት ቢሆንም እስከ ጥር 2013 ዓ.ም 6.2% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤

86. በተመሳሳይ ሁኔታ የግድብ ግንባታ እና ተያያዥ ውቅሮች /Dam and Appurtenant structures/ ስራን ከሚያከናውነው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ጋር ኮሚሽኑ ውል የተፈራረመው ሰኔ 17 ቀን 2011 (June 24, 2019) ቢሆንም የግንባታ ስራ የጀመረው ዘጠኝ /9/ ወር ከዘገየ በኋላ ሚያዚያ 2012 (April 2020) ሲሆን በአሁኑ ወቅት የፕሮጀክት አፈፃፀሙ 50% መድረስ የነበረበት ቢሆንም እስከ ጥር 2013 ዓ.ም ድረስ ያለው አፈፃፀም 19.61% ብቻ መሆኑ፤

<u>በጉምሩክ ኮሚሽን የኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

87. ኮሚሽኑ የኮንትሮባንድ ንግድ በሚመለከት መረጃዎችን ሊያሰባስብ፣ ሊያደራጅ፣ ሊተነትን እና በማዕከላዊ የመረጃ ቋት /በዳታ ቤዝ/ የተደገፈ መረጃ ሊኖረው እንዲሁም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሊያደርግ ሲገባ የኮንትሮባንድ ንግድን በሚመለከት ማን ህገ ወጥ ስራ እንደሰራ፣ የት፣ መቼና እንዴት የሚሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ውጤታማ ከማድረግ አንፃር የኢንተለጀንስ ባለሙያዎች በሙያው የበለፀጉ አለመሆንና የአቅም ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣ የሚመለከታቸው በአንዳንድ የፀጥታ አካላት በመረጃዎች ላይ እምነት ያለመኖር እና መረጃዎች በመረጃ ቋት እና በዳታ ቤዝ /ኮምፒዩተራይዝድ/ በሆነ መልኩ አለመያዛቸው፣ በተገቢው ሁኔታ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት አለመኖሩ፣ በተጨማሪም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ከኮሚሽን መ/ቤቱ ጋር የኮንትሮባንድ ንግድን በሚመለከት መረጃዎችን በonline system የሚገናኙበት ተገቢው የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፤

88. ኮሚሽኑ የኮንትሮባንድ እቃዎችን ለሚጠቁሙ፣ ለሚይዙ፣ ድጋፍና ትብብር ለሚያደርጉ አካላት አስፈላጊውን የወሮታ አበል ክፍያ የሚከፍልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም የወረታ አበል ክፍያ ስርዓት አበረታች ያለመሆን፤ የክፍያ ሂደቱ ረጅም ጊዜ የሚወስድና የሚዘገይ በመሆኑ እና ጠቋሚዎቹ መረጃ እየሰጡ አለመሆኑ፤

89. ኮሚሽኑ የኮንትሮባንድ ንግድ በማህበረሰብ ጤና፣ በአገር ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና አካባቢ ላይ የሚያሳድረውን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ሲገባ ኮንትሮባንዲስቶች ለህብረተሰቡ የጤና ጠንቅ የሆኑ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን የሰውና የእንስሳት መድሐኒቶችን፣ አደንዛዥ እፆችን፣ የታሸጉ ፈሳሽና ደረቅ ምግቦችን፣ በአገር ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ህገ ወጥ የገንዘብና የጦር መሳሪያዎችን የሚያዘዋውሩበት፣ አስፈላጊው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው እቃዎችና የከበሩ ማዕድናትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡበትና ከአገር የሚያስወጡበት ሁኔታ መኖሩና ኮሚሽኑ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል የተቀናጀና የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱና አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን፤

90. ኮሚሽኑ የኮንትሮባንድ ንግድ የፍሰቱን መነሻ፣ መተላለፊያና ማከማቻ ቦታዎችን በመለየት ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ሲገባ የኮንትሮባንድ ፍሰቱን፣ መተላለፊያ፣ ማከማቻና ማከፋፋያ ቦታዎችን በተመለከተ በየወቅቱ በቂ ጥናት አለማድረግና በጥናቶቹ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር አስተማሪና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ወደ ተጨባጭ ውጤት መቀየር አለመቻሉ፤

91. እንዲሁም ኮሚሽኑ በህገ ወጥ ተጠርጣሪዎች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር /ከክልል አቃቤ ህግና ፓሊስ/ በተገቢው ሁኔታ እየሰራ አለመሆኑና የራሱ የሆነ አቃቤ ህግ እና ኮንትሮባንዲስቶችን ወይም ተጠርጣሪዎችን የሚመረምርበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፣ ተጠርጣሪዎችን ለክልሉ በሚሰጥበት ወቅት ተገቢውን ፍርድ /ቅጣት/ ሳያገኙ የሚለቀቁበትና በዘርፉ ስራ ላይ ተመልሰው የሚሰማሩበት ሁኔታ መፈጠሩ፤ ኮንትሮባንዲስቶች አገሪቱን የሚጎዱ የጦር መሳሪያዎችን፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው

መድሐኒቶች፣ መጠጥና ምግቦችን፣ አደንዛዥ እፆችንና የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመባቸው የኮንትሮባንድ እቃ ጭነው በሚገኙት ላይ የሚጣለው የ100,000 ብር ቅጣት በቂ፣ አስተማሪ፣ ኢኮኖሚያቸውን ሊያቀጭጭ የሚችል አለመሆኑ፣ ህገ ወጦቹ በተደጋጋሚና በተለያየ ወቅት ቅጣቱን እየከፈሉና በዘርፉ ስራ ላይ ተመልሰው ተሰማርተው የሚገኙበት ሁኔታ መኖሩና ህገ ወጥ ግለሰቦች በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ የኮንትሮባንድ እቃዎችን ከሃገር የሚያስወጡበት፣ ወደ ሃገር ውስጥ የሚያስገቡበት፣ ለህብረተሰቡ የሚያከፋፍሉበትና የሚያሰራጩበት ሁኔታ መኖሩና ኮሚሽኑ ችግሩን ከምንጩ ለመቀነስ ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ እና ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን፤

92. ኮሚሽኑ በኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥር ስርዓቱ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡና ከአገር የሚወጡ ማጓጓዣዎችን ከተወሰነው/ከተፈቀደላቸው/ የጉዞ መስመር ውጭ እንዳይንቀሳቀሱ፣ እንዳያቆሙ፣ እንዳያወርዱና እንዳያራግፉ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ከአገር የሚወጡ ማጓጓዣዎች ከመነሻ እስከ መዳረሻ ቦታዎች በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠም የካርጎ ትራክንግ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር፤

<u>በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የንብረት አስተዳደር አፈፃፀም ውጤታማነት በተመለከተ</u>

93. አገልግሎቱ ንብረቶችን የሚያስተዳድርበት የአፈፃፀም መመሪያዎች ሊያወጣ እና በመመሪያው መሠረት መከናወኑን ሊያረጋግጥ የሚገባ ቢሆንም፤ በኦዲት ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው አገልግሎቱ በ2006 ዓ.ም. ንብረቶችን የሚያስተዳድርበት ፖሊሲ እና መመሪያ ያዘጋጀ ቢሆንም በናሙና በታዩት በጎፋ ማእከላዊ እቃ ግምጃ ቤት፣ በኮተቤ የተሽከርካሪ ጥገናና የትራንስፖርት አስተዳደር፣ በምዕራብ እና በደቡብ አዲስ አበባ ዲስትሪክቶች የእቃ ግምጃ ቤቶች ያሉ ሥራ ፈጻሚ ሰራተኞች የደረሳቸው ፖሊሲም ሆነ መመሪያ አለመኖሩ፤

94. በተጨማሪም በ2011 ዓ.ም. የተሽከርከሪ አጠቃቀም መመሪያ የወጣ ቢሆንም በመመሪያው አንቀጽ 10.1.16 ሁሉም ተሽከርካሪዎች የኪሎሜትር መቆጣጠሪያ /ጌጃቸው/ እንዲሰራ መደረግ አለበት ቢልም በመ/ቤቱ 90 በመቶ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፣ በአንቀጽ 10.1.14 መሰረት ተሽከርካሪዎች በአይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር ሊጓዙ እንደሚችሉ በየጊዜው የመስክ ጥናት መደረግ እንዳለበት ቢገለጸም የመስክ ጥናቱ አለመደረጉ፣ በአንቀጽ 10.1.1 መሰረት የስምሪትና ነዳጅ ቁጥጥር መዝገብ (ሎግ ቡክ) እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ ይኖርበታል ቢልም የማይመዘገብ መሆኑ፣ በአንቀጽ 19.2 በክልል የተመደቡ ተሽከርካሪዎችን ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ጋር በመሆን አጠቃላይ ቁጥጥር መደረግ አለበት ቢልም አልግሎቱ ቁጥጥሩን እያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

95. በአገልግሎቱ ንብረቶችን በዓመት አንድ ጊዜ ሊቆጠሩ እንዲሁም ውድ ዋጋ ያላቸውን፣ በቀላሉ ሊወሰዱ የሚችሉ እና በፍጥነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ንብረቶች ድንገተኛ ንብረት ቆጠራ ሊደረግ፣ በንብረት ቆጠራ ወቅት በሚገኙ ልዩነቶች እና ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው በአገልገሎቱ ውድ ዋጋ ያላቸው፣ በቀላሉ ሊወሰዱ የሚችሉ እና በፍጥነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ንብረቶች ድንገተኛ ቆጠራ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት አለመኖሩ ዓመታዊ ቆጠራ የሚከናወን ቢሆንም ቆጠራ የማይደረግባቸው ንብረቶች መኖራቸው፤

96. አገልግሎቱ በሥሩ ያሉ ንብረቶችን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጡ ደህንነታቸው እንዲጠበቅና ተገቢ እንክብካቤ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ከቀረቡ ቃለ መጠይቆችና በአካል ምልከታ እንደታየው በጉፋ በሚገኘው የማእከላዊ እቃ ግምጃ ቤት፤ በምእራብ እና በደቡብ አዲስ አበባ ዲስትሪክቶች የተለያዩ አይነት፣ መጠናቸው ብዙ የሆነ እና ከፍተኛ ገንዘብ የወጣቸባቸው ንብረቶች (ሃይቴንሽን ሁክ፣ ትራንስፎርመሮች፣ ሳፖርት ብሬከሮች፣ ለመንገድ መብራት የሚሆኑ እቃዎች፣ ብሎኖች፣ ፑሊዎች፣ አሬስተሮች፣ ኬብሎች) ለደህንነታቸው በሚያሰጋ መልኩ በየሜዳው ተበታትነው የሚገኙ መሆናቸው፣

97. በአገልግሎቱ የሚገኙ ንብረቶች እንዳይጠፉ እና እንዳይሠረቁ አስፈላጊው ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ ቢሆንም፤ በናሙና በታዩት በማእከላዊ እቃ ግምጃ ቤት እና በተሽከርካሪ ጥገናና ትራንስፖርት አስተዳደር ከግቢ ስፋት እና ከንብረቶች አቀማመጥ ወይም እቃዎች ተበታትነው በየቦታው ከመቀመጣቸው አንጻር ለመጠበቅ የማይመቹ ከመሆኑም በላይ በተሽከርካሪ ጥገናና ትራንስፖርት አስተዳደር በቂ መብራት እና ከጀርባቸው የጥበቃ ቤት የሌለ በመሆኑ፤ በደቡብ እና ምዕራብ አዲስ አበባ ዲስትሪክቶች አጥራቸው ያልተጠናከሩ በመሆናቸው በርካታ ንብረቶች ለብክነትና ለዘረፋ የተጋለጡ መሆኑ፤

<u>በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የግል የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን በተመለከተ</u>

98. በሚኒስትሮች ም/ቤት የወጣውን ደንብ ቁጥር 206/1987 ሥራ ላይ ለማዋል የሚያግዙ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ከመንግስት ባለቤትነት ውጭ የሚቋቋሙ የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥ እና እድሳት መመሪያ ሊያዘጋጅና አፈጻጸሙን ሊከታተል የሚገባ ቢሆንም የግል የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፈቃድ አሳጣጥ እና ዕድሳትን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀ መመሪያ አለመኖሩ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ፈቃድ የሚሰጡና የሚያድሱ አካላት መከተል የሚገባቸው መሪ የሆነ የግል የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ስታንዳርድ ካለመኖሩም በላይ የርቀት ትምህርትን ሊመራ እና ሊያስተዳድር የሚችል ምንም አይነት ህግና መመሪያ የሌለ፤ በመዋቅር ደረጃም ቢሆን፤ ይህንን ሥራ በባለቤትነት የሚከታተል ክፍል ያልተደረጀ መሆኑ፣

99. ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተገነቡ በህንጻ አዋጁ የተቀመጡትን መስፈርቶች (የእሳት ማጥፊያ፣ የአደጋ ጊዜ መውጫ ወዘተ ያላቸው) ያሟሉ መሆናቸው ሊረጋገጥ የሚገባ ቢሆንም በናሙና ከታዩት 22 የግል አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪውን እና የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ ከሦስት ት/ቤቶች በስተቀር ቀሪዎቹ 19 ትምህርት ቤቶች የሌላቸው ከመሆኑም በላይ በሁሉም የትምህርት ተቋማት በህንፃዎቻቸው ላይ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌላቸው መሆኑ፤

እንዲሁም ትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና፣ ጥራት የሙ-ያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን በመከታተያ ቼክ ሊስቱ ውስጥ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች መኖራቸውና በየወቅቱ የሚሞሉ መሆኑን እንዲሁም የህንፃዎች የአደጋ ጊዜ መውጫ በት/ቤቶች ውስጥ ስለመኖሩ የሚረጋገጥበት መስፈርት የሌላ መሆኑ፤

100. ትምህርት ቤቶች በተቀመጠው ደረጃ መሰረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት መያዛቸው እና በአጥር የተከበቡ መሆናቸው እንዲሁም በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቤተ መፅሀፍት፣ ቤተ ሙከራ፣ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል፣ የስፖርት ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን (መፀዳጃ፣ ውሀ) ማሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚገባ ቢሆንም፤ በናሙና በመምረጥ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው 22 የግል የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በተቀመጠው ደረጃ መሰረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት መያዝ የሚገባቸውን ያሟሉ አስራ አራቱ ት/ቤቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ስምንቱ (36%) ተፈላጊውን የቦታ ስፋት ያላሟሉ መሆናቸውን፣ ሁሉም ት/ቤቶች ከአዋኪ ነገሮች 500 ሜትር ይራቁ የሚለውን መስፈርት የማያሟሉና በት/ቤቶች አካባቢ በመስፈርቱ የተከለከሉ አገልግሎት ሰጪዎች (ጋራዥ፣ የመዝናኛ ቦታዎች፣ የትራፊክ እንቅስቃሴ፣ የመሳሰሉት) መኖራቸውን እንዲሁም አስራ ሰባቱ ት/ቤቶች (77%) ቤተ-መጽሐፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል፣ የስፖርት ሜዳ በስታንዳርዱ በተቀመጠው መሰረት ያላሟሉ መሆናቸውን፣

101. በ1987 ዓ/ም የተዘጋጀ የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ላይ መምህራን በማንኛውም የትምህርት ደረጃ ላይ ለማስተማር የሙ-ያ ብቃት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው የተገለፀ ቢሆንም ከ26 ዓመት በኋላም የመምህራን የሙ-ያ ብቃት ምዘና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

102. በተጨማሪም በአጠቃላይ ትምህርት የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ በስታንዳርድ 3 ላይ ሁሉም የት/ቤት ርዕሰ መምህራን እና መምህራን የሙ-ያ ፍቃድ እና ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ ሊኖራቸው እንደሚገባ የተገለፀ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና ተመርጠው በታዩት የግል የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ኢንተርናሽናል ት/ቤቶች ላይ ምንም አይነት የሙ-ያ ብቃት ምዘና የወሰደ መምህር አለመኖሩን፣

103. የግል የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት ትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት ላይ በመመስረት መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት አለም አቀፍ ት/ቤቶች ምን አይነት የትምህርት ካሪኩለም መጠቀም እንዳለባቸው የሚያሳይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ግልፅ የሆነ መመሪያ እና ስታንዳርድ የሌለ ሲሆን የአጠቃላይ ትምህርት የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ መመሪያ ላይ መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአገር አቀፍና በክልል የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶችን ያገናዘበ መሆን እንዳለበት በስታንዳርድ 17 ላይ የተገለፀ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርትና ስልጠና ጥራትና ሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን በ2011 እና 2012 ዓ/ም ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ባሉ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ የትምህርት ተቋማት በተከናወነ የውጭ ኢንስፔክሽን ትንተና መሰረት በአንደኛ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (ከደረጃ 1-3 ባሉት) ላይ የስታንዳርዱ አፈፃፀም ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን እና ይህንን ለማስተካከል የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን፤

<u>በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከመንግሥት በጀት የሚመደብ የምርምር በጀት (Fund) አስተዳደር ስርዓት</u>

104. ዩኒቨርሲቲው ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የምርምር አካባቢዎችን (priority areas) ሊለይ እና ምርምር ሊያካሂድ እንዲሁም የተለዩትን አካባቢዎችም በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲው ቅድሚያ የሚሰጣቸው የጥናትና የምርምር አካባቢዎችን (priority areas) የለየ ቢሆንም የተለዩት አካባቢዎች ሁሉን አቀፍ (compherhensive) አለመሆናቸው፣ የምርምር አጀንዳ አያያዝ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የምርምር ሃሳቦች ልየታው ክፍተት ያለበት (Poor research agenda setting and prioritization) ስለመሆኑ በዩኒቨርሲቲው (2013-2022 E.C) ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ የተገለፀ ከመሆኑም ሌላ ዩኒቨርሲቲው ለሚያካሂዳቸው ምርምሮች ቅድሚያ የሚሰጣቸውን /priority areas/ የምርምር መስኮች /ዘርፎች በየአምስት/5/ ዓመቱ ወቅታዊ የማያደርግ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው የምርምር ዘርፎች ሲለዩ ደግሞ የዩኒቨርሲቲውን ተመራማሪዎች እና ኮሌጆች ሀሳብ እንዲያቀርቡ ወይም ተሳታፊ እንዲሆኑ አለመድረጉ፤

105. ዩኒቨርሲቲው በሚመድበው ፈንድ ለሚያካሂደው ምርምር በምርምር አፈጻጸም (progress)፣ በጥራት ቁጥጥር፣ በሀብት አጠቃቀም፣ በፕሮግራም ተፅእኖ/ impact እና ውጤታማነት እና የተከናወኑ የምርምር ውጤቶች ያስገኙት ፋይዳ/Impacts በተመለከተ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም የአፈጻጸም ደረጃቸው ተገምግሞ ቀጣይ ስራዎች ይሰራሉ ቢባልም ግምገማው ስለመከናወኑ ማስረጃ እና የግምገማ ሪፖርት ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ የተቀናጀ ምርምርን በተመለከተ የአፈጻጸም፣ የክትትልና ግምገማ (Research Projects performance Monitoring and Evaluation) ከባለድርሻ አካላት ለማካሄድ ታቅዶ አለመከናወኑ፣

106. ለሴት ተመራማሪዎች የጥናትና ምርምር ቦታዎችን በመለየት እና በማመቻቸት ልዩ ድጋፍ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ከታየው መረጃ ከ2009-2012 ዓ.ም ቴማቲክ(Thematic) ምርምር ዘርፍ በሴት ተመራማሪዎች የተከናወነው (10.71%) እና በችግር ፈቺ ምርምሮች ደግሞ (14.5%) በመሆኑ በአጠቃላይ ከሚከናወኑ ምርምሮች አንፃር የሴቶች የምርምር ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑ፣

107. በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የምርመር ሥራዎች በመጀመሪያ ሲመረጡ እናስገኘዋለን ብለው ያቀረቡትን ውጤት ያሳኩ ስለመሆናቸው እና ተግባራዊ ተደርገው የምርምሩ ተጠቃሚዎችና የህብረተሰቡን ጥያቄን ምላሽ የሰጡ መሆናቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ተጠናቀው የወጡ የምርምር ሥራዎች ያስገኙት ፋይዳ ሊገመገም የሚገባ ቢሆንም ወቅታዊ ችግሮችን መሰረት ያደረጉ የምርምር ውጤቶች ተከናውነውና በወቅቱ ታትመው መደርደሪያ ላይ ከማስቀመጥ ባለፈ ለሚመለከታቸው ኢንዱስትሪና ለማህበረሰቡ እንዲደርሱ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ዩኒቨርሲቲው የበኩሉን ዘላቂ ጥረት የማያደርግ በመሆኑ በዩኒቨርሲቲው የተሰሩ አብዛኞቹ ምርምሮች ሀገራዊ ልማት ላይ አስተዋጽኦ ስለማድረጋቸው ያልተገመገመ መሆኑ፤

108. ዩኒቨርሲቲው የሚያከናውናቸው ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን፣ የፕሮጀክት ሀሳቦችን፣ ለምርምሩ የወጡ የተለያዩ ወጪዎችን፣ ሪፖርቶችን፣ ግምገማዎችን እና ህትመቶችን በተመለከተ የተደረጃ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ለህትመት እና ለምርምር ውጤት አስተዳደር የመረጃ ቋት እጥረት መኖሩ፤ (Lack of database for publication and research output

management.) የጥናትና ምርምር መረጃ አያያዝ ስርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ የምርምር ጆርናሎች ለሌላቸዉ የምርምር መስኮች ውጤቶቹ የሚታተሙበት አዳዲስ ጆርናሎች እንዲቋቋሙ የታቀደ ቢሆንም እንዲቋቋም አለመደረጉ፣

109. ዩኒቨርሲቲው በአገር ውስጥ ካሉ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት የምርምር ሥራዎች መስራቱን እና የምርምር አካባቢዎች ድግግሞሽ እንዳይኖር በጋራ ሊጠቀሙባቸው የሚያስችላቸውን የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በአገሪቱ ከሚገኙ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር የምርምር ድግግሞሽ እንዳይኖርና ተያያዥ የሆኑ የምርምር ሥራዎችን በጋራ ለመስራት በሚያስችል መልኩ መረጃን የመለዋወጥ እና የመያዝ ሥራ አለማከናወኑን በናሙና ከታዩ ኮሌጆች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ የተቻለ መሆኑ፤

<u>የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ (ICT PARK) አፈጻጸም በተመለከተ</u>

110. ፓርኩ በሀገራችን በአይሲቲ ዘርፍ የመጀመሪያው ፓርክ እንደመሆኑ መጠን፤ መንግስት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ከመስጠቱ አንፃር የሀገሪቱን ስትራቴጂክ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በመሆን እንዲቋቋም ያደረገው በመሆኑ ፓርኩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀትና ዕቅዱን በየዓመቱ በመሸንሸን ሊያቅድና አፈጻጸሙን በየጊዜው ሊገመግም ሲገባው በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ፓርኩ የተሰጠውን ተግባር በአግባቡ ለመፈጸም ይረዳው ዘንድ ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ያላጸደቀ መሆኑን እንዲሁም ፓርኩ እንደ ጽ/ቤት ዕቅድ የማያዘጋጅ በመሆኑ የፓርኩ ባለሙያዎችም ስራዎችን ለመስራት በመቸገራቸው በራሳቸው ተነሳሽነት በግላቸው ዕቅድ በማቀድ እየሰሩ ከመሆኑም በላይ ፓርኩ የሚሰሩ ስራዎችን በየጊዜው የማይገመግም መሆኑ፤

111. በፓርኩ ውስጥ ዘመናዊ የቴሌኮምኒኬሽን የዳታ ማዕከል መሰረተ ልማት (ብሮድባንድ ኢንተርኔት፣ ኢሜል፣ ስቶሬጅ፣ የሆስቲንግ፣ የቪዲዮ ኮንፍረንስ ወዘተ) በማስፋፋት እና

የዲጅታል ላይብረሪ በማቋቋም ለፓርኩ ተጠቃሚዎች አገልግሎት ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም ፓርኩ እነኚህን አገልግሎት እየሰጠ ያለመሆኑ፤

112. ፓርኩ በአይሲቲ ማኑፋክቸሪንግ እና ሶፍትዌር ኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ እና መሰማራት ለሚፈልጉ ድርጅቶች ምርታቸውንና አገልግሎታቸውን በማሳደግ ለ ውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ እና የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ አስፈላጊውን ድጋፍ (ማለትም በቂ መብራትና ውሃ አቅርቦት፣ በቂ ዳታ ሴንተር አገልግሎት፣ የኪራይ ቦታ፣ የመመገቢያና የመዝናኛ ቦታ እና የትራንስፖርት አገልግሎት) ሊያቀርብ የሚገባ ቢሆንም ከ2008 — 2010 በጀት ዓመት የተወሰኑ ድርጅቶች በአይሲቲ ማኑፋክቸሪንግ እና ሶፍትዌር ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የገቡ ቢሆንም ፓርኩ ማሟላት ያለበትን ባለማሟላቱ ከ1 ድርጅት በስተቀር ወደ ማልማት ስራ ያልገቡ መሆኑ፤

113. እንዲሁም በአይሲቲ ማኑፋክቸሪንግ እና ሶፍትዌር ኢንዱስትሪ ልማት ለመሰማራት መሬት በመውሰድ ግንባታ የጀመሩ እና ግንባታ ለመጀመር አጥር ካጠሩት ውስጥ የሲ-ኔት ሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ካምፓኒ (CNET Software Technology Plc) ህንጻው መሰረት (Basement) እና አንደኛ ወለል ላይ ደርሶ የተቋረጠ ሲሆን ድርጅቱ ለምን እንዳቋረጠ እንዲሁም አጥር አጥረው ወደ ስራ ያልገቡ ሌሎች ድርጅቶችን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ወደ ስራ ለማስገባት ባለመቻሉ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የህንጻ ግንባታዎች እንደተቋረጡና በአጥር ተከልለው እንዳሉ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

<u>በኢሚግሬሽን፤ዜግነት ጉዳይና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

114. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር.449/2011 መሠረት ወቅታዊና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓትን በጥናት ሊለይ፤ ሊመርጥ፤ አደረጃጀቱንና አሰራሩን ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ወቅታዊና በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ አደረጃጀቱንና አሰራሩን ያልዘረጋ እንዲሁም የምዝገባ ቴክኖሎጂን በጥናት ለይቶ ያልመረጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠ ከታዩት የክልል፣ የከተማ አስተዳደሮችና የቀበሌ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ከተደረገው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. በኤጀንሲው የመቋቋሚያ ደንብ ቁ.449/2011) አንቀጽ 5/13 ኤጀንሲው የዜጎችን መረጃ ደህንነት ለመጠበቅ በሚያስችል ቦታ ሊያደራጅ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ የወሳኝ ኩነት መረጃ በቴክኖሎጂ ባለመታገዙ፣ በቂ ቢሮና የሰው ኃይል ባለመኖሩ፣ መረጃው ከመዝጋቢ አካላት መጥቶ መረጃ ቅበላ ክፍል ገብቶ፣ ተጣርቶ ቋሚ መረጃ ማደራጃ ክፍል እስኪገባ ድረስ ባለው ሂደት፤ በተጨማሪ የኩነት ስራዎች የማንዋል ስራ ስለሆኑና መረጃዎች ብዙ በመሆናቸው እንዲሁም በየቦታው የሚቀመጡ በመሆናቸው ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ አዳጋች ያደረገው መሆኑ፤

116. ኤጀንሲው ተልዕኮውን ለማሳካት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን በመለየት፤ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊነቱን በጋራ ሊከታተል ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው የመንግስትና ሌሎች ተቋማት ጋር ማለትም (ከጤና ሚኒስቴር፣ በተዋረድ ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር) ከሴቶች እና ህጻናት ፣ ከሀይማኖት ተቋማት ጋር፣ ከአዋላጅ ጤና ባለሙያ ማህበራት ጋር ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ የፈረመ ቢሆንም፤ ተግባራዊነቱን ተከታትሎ ያላስፈጸመ መሆኑ፤

<u>በሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመንግስት ተቋማት የኮቪድ 19 ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚደረገውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈጻጸም በተመለከተ</u>

117. የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎች ለማስፈጸም የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች በመንግስት ተቋማት ተዘርግተው ስለአፈጻጸሙ ክትትል ሊደረግ ይገባል

118. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በፌደራል ትርንሰፖርት ባለስልጣን ስር በሚገኙ የአገር አቋራጭ መናሃሪያዎች (ላምበረት፣ ቃሊቲ፣ አዲስ ከተማ አነስተኛ እና መለስተኛ መናሀሪያዎች) እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ የህዝብ ትራንስፖርት በሚሰጡ ቃቋማት በተደረገዉ ምልከታና በተዳሰሱ ሪፖርቶች መመሪያዎች ያለመኖና ቢኖርም በሚፈለገዉ መልኩ ተግባራዊ አለመሆኑ፤

119. በተጨማሪም የመንግስት የልማት ድርጅቶ ሰራተኞችና ተገልጋዮች የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢም በጤና ሚኒስቴር ባለሙያዎች በተቀመጠው ምክረ-ሃሳብ መሰረት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛን አለመጠቀም፤ ርቀትን አለመጠበቅ፣ በየጊዜው እጅን በውሃና በሳሙና አለመታጠብ፣.. ወዘተ ችግሮች መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኢትዮጵያ የአክሪዴትሽን ጽ/ቤት የላብራቶሪ እና የመመርመሪያ መሳሪያዎች አክሬዲቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ

120. ፅ/ቤቱ አክሪዴትድ ሳይደረጉ የተሰማሚነት ምዘና በሚሰሩ አካላት ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ የሚገባው ቢሆንም በላብራቶሪ የሥራ መስክ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ የሚሰጡ የመንግስት ተቋማት (ግብርና ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር…) ለአክሬዲቴሽን ልዩ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ፤

121. በሌላ በኩል ፅ/ቤቱ በየአመቱ ክትትል የሚያርግ ቢሆንም በመ/ቤቱ መቋቋሚያ ደንብ መሰረት ድንገተኛ ፍተሻ ያላከናወነ ከመሆኑም በላይ በአገሪቱ ብቸኛ በሆነው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብሔራዊ ሪፈረንስ ላብራቶሪ (EPHICCRL) ላይ ክትትል ለማድረግ በተደጋጋሚ ያቀደ ቢሆንም ተግባራዊ አለማድረጉ፣

122. በተጨማሪም በፍተሻና በካሊብሬሽን ላቦራቶሪ (ISO/IEC 17025) የመስክ (on-site) ግምገማ ለማካሄድ እቅዶ በ2010 (0%)፣ 2011 (48%) እና 2012 (18%) ብቻ የመስክ (on-site) ግምገማ ያካሄደ በመሆኑ የእቅድ ክንዉን አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤ የሕክምና ላቦራቶሪ (ISO:15189) በተመለከተ የመስክ (on-site) ግምገማ ለማካሄድ እቅዶ በ2010 (25%)፣ 2011 (66%) እና 2012 (38%) ብቻ የመስክ (on-site) ግምገማ ያካሄደ በመሆኑ የእቅድ ክንዉን አፈጻጸሙ በተመሳሳይ መልኩ ዝቅተኛ መሆኑ፤

123. አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማት ባገኙት የአክሬዲቴሽን ወሰን ላይ ብቻ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱም ተቋማት አክሪዴትድ በሆኑበት ወሰን ላይ ብቻ እየሰሩ መሆናቸውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ማረጋገጥ የሚገባ ቢሆንም ብለስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ ሰርቪስ ኃ/የተ.የግ.ማ በ150 አይነት የፍተሻ ላብራቶሪ እየሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ15 የፍተሻ አይነት በ10% የፍተሻ ወሰን ላይ ብቻ አክሬዴትድ መሆኑ፣ እንዲሁም በምርት ሰርቲፊኬሽን ላይ

አክርዲቴሽን ሳይኖረው ለ17 ድርጅቶች የምርት ሰርቲፊኬሽን የሰጠ መሆኑን፤ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በ2577 አይነት የፍተሻ ላብራቶሪ የሚሰራ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በኬሚካል፣ በማይክሮባይሎጂ፣ በኤሌክትሪካል እና በጨርቃጨርቅ (textile) ዘርፍ በ40 የፍተሻ አይነት በ7% የፍተሻ ወሰን ላይ ብቻ አክሬዴትድ መደረጉ፤ ቤተዛታ ሜዲካል ላብራቶሪ በኬሚስትሪ እና በሔማቶሎጂ የሜዲካል ላብራቶሪ የፍተሻ አይነት ላይ ብቻ አክሬዴትድ የሆነ ሲሆን በሌሎች አክሬዴትድ ባልሆነበት Microbiology; Hormonal analysis; Pathology; Monoculare; Sampel collection; Referral test and Uria test የሜዲካል ላብራቶሪ የፍተሻ አይነት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፣ አለርት ሆስፒታል ሜዲካል ላብራቶሪ ሔማቶሎጂ ላይ ብቻ አክሬዴትድ ሲሆን በሌሎች Grainstain; CBC; CD4; AFB የሜዲካል ላብራቶሪ የፍተሻ አይነት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፣ ሳንቴ ሜዲካል ላብራቶሪ በHematology እና በClinical Chemistry ወሰን ላይ ብቻ አክሬዴትድ ሲሆን አክሪዴትድ ባልሆነበት Bacteriology የሚዲካል ላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፣

124. ፅ/ቤቱ አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማት በቀጣይነት ብቃታቸውን ማረጋገጣቸውንና የተቀመጡ መስፈርቶችን የማሟላት ሃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ሊያረጋግጥ እና የአክሬዲቴሽን ምልክት ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ክትትል ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ 8 የተስማሚነት ምዘና ተቋማት አራቱ (ኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ ብለስ አግሮ ፉድ ላብራቶሪ ሰርቪስ ድርጅት፣ ብሔራዊ አልኮል እና አረቄ ፋብሪካ እና ሳንቴ ሜዲካል ላብራቶሪ) አክሬዴትድ የሆኑባቸውን እና ያልሆኑባቸውን የፍተሻ አይነት ሪፖርት አንድ ላይ በማዘጋጀት ምልክቱን ለሁለቱም የሚጠቀሙ ሲሆን ሁለቱ (አለርት ሴንተር ክሊኒካል ላብራቶሪ እና ቤተ-ዛታ ሜዲካል ላብራቶሪ) አክሬዴትድ በሆኑበት ወሰን ላይ የአክሬዴቴሽን ምልክት የማይጠቀሙ መሆኑ፣

125. ፅ/ቤቱ ከውጪ አክሬዴቴሽን አገልግሎት ለማግኘት የሚጠይቁ ተማቋትን ለመገምገም ከውጭ በጊዜያዊነት ባለሙያ የሚቀጥር ሲሆን የሚቀጠረው ባለሙያ (Assessor) ብቃትን ለማረጋገጥም ሆነ ገለልተኛነታቸውን ለማረጋገጥ፤ የጥቅም ግጭት (conflict of interest) እንዳይኖር የሚያጣራበት እና የሙያ ብቃታቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚመርጥበት

ሥርዓት ስለመዘርጋቱ እና በፅ/ቤቱ የአሰሰር(Assessor) ባለሙያ የሚቀጠርበት መመዘኛ መስፈርት ስለማውጣቱ በኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ወቅት ማስረጃዎቹ ተጠይቀው ሊያቀርብ አልቻለም፡፡

በስራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን ለሥራ ዕድል ፈጠራ የተዘረጋው ቅንጅታዊ አሠራር እና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ

126. ኮሚሽኑ በአገሪቱ በየዓመቱ ለሚፈጠረው ለሥራ ዕድል ፈጠራ ድጋፍ የሚውል በ2012 በጀት ዓመት 384,900,000.00 ዶላር፣ በ2013 በጀት ዓመት የ6 ወር 217,337,936.00 ዶላር በድምሩ 602, 237,936.00 ዶላር የሰባሰበ ቢሆንም፤ ከተሰበሰበው ፈንድ ውስጥ ምን ያህሉ ክልሎችን ለመደገፍ እንደዋለ፣ እንዴት ለክልሎች እንደሚከፋፈል መስፈርት ስለመኖሩና በመስፈርቱ መሰረት ስለመከፋፈሉ እና ለታለመለት ዓላማ የዋለ መሆኑን ክትትል ስለመደረጉ የሚገልጽ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ፤ ያልቀረበ መሆኑ፡

127. ኮሚሽኑ የሥራ ዕድል ፈጠራን ለማስፋፋት የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግስት አካላት፤ የግል ዘርፉ፣ መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ (Informal Sector)፣ የልማት አጋሮች እና ተቋማት በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም፤ ከፌዴራልና ክልል መንግስት አካላት በስተቀር ከግሉ ዘርፍ፤ መደበኛ ካልሆነው ዘርፍ (Informal Sector)፣ የልማት አጋሮችና ተቋማትን በማስተባበርና በመደገፍ የሥራ ዕድል ፈጠራን ለማስፋፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ፤

128. ኮሚሽኑ ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ሥልጠናዎች እና የሥራ ልምምድ ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ የሚችልበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ኮሚሽኑ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት የሥልጠና ተቋማትን እና ሥራ ፈላጊዎችን በማማከር በተገቢው ሁኔታ ከሥራ ገበያው ጋር የሚጣጣሙ ሥልጠናዎች እና የሥራ ልምምድ መኖራቸውንና የሥራ ላይ ልምምዶቹ ውጤታማ መሆናቸውን ያላረጋገጠ መሆኑ፤

129. ኮሚሽኑ የሥራ ዕድል ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን አካል ጉዳተኞች ከሚከናወኑት የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ያገኙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት

ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባው ቢሆንም በስትራቴጂክ ዕቅድና ኢትዮጵያ ትሰራለች በሚል ፕሮጀክት በአካታች ፕሮግራም (በ2013-2017) ሥራ ለመፍጠር በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በተሰጠው ስልጣንና ተግባር በአገሪቱ የሚገኙትን የሥራ ዕድል ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን አካል ጉዳተኞች ምን ያህል እንደሆኑ በመለየትና ባላቸው ክህሎት መሰረት ወደ ስራ ለመግባት የሚችሉበት ድጋፍ እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበርን በተመለከተ</u>

130. አገራዊ የክትመት ስርዓትን ለመምራት የሚያስችል አገራዊ ስፓሻል ፕላንን መሰረት በማድረግ ክልሎች የከተሞቻቸውን ፕላን እንዲያዘጋጁና ተግባራዊ እንዲያደርጉ በፌዴራል ደረጃ አስፈላጊ የሆነ የስራ መዘርዝር፣ በጀት ማፈላለግ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም በሁሉም ደረጃ ያሉ አመራሮችም ሆኑ ባለሙያዎች በስራው ላይ በቂ የጋራ ግንዛቤ ይዘው ወደ ስራ ባለመግባታቸው እስካሁን የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን እና የከተሞች ክላስተር ልማት ፕላን ተግባራዊ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ድጋፍ ያላደረገ ስለሆነ በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጀው ስፓሻል ፕላን ወደ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ወርዶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤ እንዲሁም ክልላዊ የከተማ ልማትና የህዝብ አሰፋፈር ፕላን በክልሎች አለመጀመሩ፣

131. የከተማ ፕላን ሲታቀድ የከተማዎቹን የኢኮኖሚ እድገትና የህዝብ ብዛት ትንበያ መነሻ በማድረግ የፊዚካል፣ ስፓሻል፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚዊ ዕቅድን ባካተተ መልኩ ሊዘጋጅ እና ሊተገበር የሚገባ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩ የባህርዳር፣ የፍኖተሰላም፣ የአዳማ፣ የድሬዳዋ የሐዋሳ እና የአዲስ አበባ ከተሞች በፕላን ዝግጅቱ ወቅት ለከተሞቹ ሶሺዮ-ኢኮኖሚ መረጃ ትኩረት በመስጠት በፕላኑ እንዲካተት አለመደረጉ፣ የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ጥናቶችን አንብቦ ለፕላን ማስፈፀሚያ የመጠቀም ልምድ ዝቅተኛ መሆኑ፤

132. በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት ለመንገድ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች፣ ለአረንጓዴ አካባቢ፣ ለህዝብ የጋራ አገልግሎቶችን እና ህንፃ ግንባታ ምጣኔ መርህ (የ30፤30፤40

የመሬት አጠቃቀም) ያገናዘበ የፕላን ዝግጅት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህ ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ የሚገባ ቢሆንም ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ የተዘጋጁ የአካባቢ ልማት ፕላኖች የ30፣30፣40 የመሬት አጠቃቀም ምጣኔን ተከትሎ ያልተዘጋጁ መሆኑና የ30፣30፣40 የመሬት አጠቃቀም ምጣኔን በነባር የከተማ ክልል ውስጥ የማይተገበር መሆኑ፣

133. የከተሞች ፕላን ሲዘጋጁ በአጎራባች ከተሞች/ክልሎች መካከል የተቀናጀና የተናበበ የከተማ ፕላን አሰራርና አፈፃፀም ሊኖር ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህ የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በአገር አቀፍ፣ በክልልና በከተማ ትስስር ደረጃ ፕላን ሳይኖር በከተማ ብቻ በታጠረ የፕላን ዝግጅት አካሄድ የሚመራ ከመሆኑም በላይ የነገዎቹ ከተሞች የሚባሉት የገጠር ልማት ማዕከላት በቁጥርም ሆነ በመጠን መበራከትና ልማታቸው በፕላን እንዲመራ የማድረግ ፍላጎት ቢኖርም ፈጣንና ዘላቂ ምላሽ ባለመሰጠቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የከተማ-ገጠር እና የከተማ -ከተማ ትስስር እንዲፈጠር አለመደረጉ፣

134. ለከተማው ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ጉልህ ሚና ያላቸው ባለድርሻ አካላት በጋራ የሚሳተፉበት የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በሁሉም ከተሞች ተቀናጅተው እንዲሰሩ የሚያስችል የተቀናጀ የከተሞች መሰረተ ልማት ማስተር ፕላን ካለመኖሩም በላይ በማስፋፊያ አካባቢ የመሬት ላይ ሽንሻኖ ከተካሄደ በኃላ መሰረተ ልማት (መንገድ፣ ውሃና መብራት) እንዲቀርብ አለመደረጉ፣ የመሰረተ ልማት አቅራቢ ድርጅት በተዘጋጀው የመንገድ የተቀናጀ የዲዛይን ስታንዳርድ መሰረት መጀመሪያ መልማት ያለባቸው አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት ተቀናጅተው አገልግሎቱን የሚያቀርቡበት የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ እና መዋቅራዊ ፕላኑንም ከማስተግበር አኳያ በከተማ አስተዳደሩና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት (ዞን አስተዳደር፣ ዞን ከተማ ልማት) የነበረው የከተማ ፕላን አፈፃፀም ቅንጅታዊ አሰራር አናሳ መሆኑ፣

135. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕላን ዝግጅትን የሚመለከቱ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶች እና ማንዋሎች በማዘጋጀት በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የተዘጋጁትም መመሪያዎች በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረጉ የሚገባ ቢሆንም

አዋጁን ተከትሎ መውጣት የነበረበት ደንብ ያልወጣ በመሆኑ ደንቡን ለማስፈጸም የሚያግዙ መመሪያዎች፣ አልወጡም፣ ስታንደርዶች እና የትግበራ ማንዋል ያልተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ የከተማ የመሬት ምዝገባ አዋጅ፣ የተቀናጀ መሰረተ-ልማት ደንብ እና የከተሞች የፋይናንስ እስትራቴጂ ለሚመለከተዉ አካል ቀርበዉ ያልፀደቁ መሆናቸው፤

በገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት ብድር ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ

136. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ብድርን በተመለከተ የብድር ፖሊሲ ሊያወጣ እና ተግባራዊ ሊያደረግ የሚገባ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የመንግስት ብድርን (የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የዋስትና ብድር) የሚመራበት የብድር ፖሊሲ ያዘጋጀና ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ፤ ተገቢውን ማስረጃ ሊያቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

137. በአለም ባንክ ብድር አስተዳደር አፈጻጸም ግምገማ (Debt Management Performance Assessment Methedology) በብድር አስተዳደር አፈጻጸም አመላካች 7 (Debt Management Performance Indicators-7) መሠረት የማዕከላዊ መንግሥት በቀጥታ ከብሔራዊ ባንክ የሚወሰደውን ብድር መጠን እና የጊዜ ገደብ በህግ መወሰን የነበረበት ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ በቀጥታ (Direct Advance) ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚወስደው ብድር የጊዜ ገደብ እና የብድሩ መጠን (Limitation) የሚገድብ ህግ ስለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ ያለመቻሉ፡

138. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየአመቱ በቀጥታ (Direct Advance) የሚወስደው ብድር የጊዜ ገደብ እና የብድሩ መጠን (Limitation) የሚገድብ ህግ ባለመኖሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለገደብ በቀጥታ ብድር (Direct Advance) የወሰዳቸው ብድሮች ተከማችተው በ2002 ዓ.ም ብር 45.87 ቢሊዮን የነበረው በ2012 በጀት ዓመት 4.19 እጥፍ በማደግ ያልተከፈለው ዋናው ውዝፍ ዕዳ 192,264,945,000.00 (አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ቢሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ሺህ) ብር መድረሱ፤

139. የመንግሥት ብድር የሰው ሀይል አስተዳደርን በተመለከተ የውስጥ ቁጥጥርን ለማጠናከር የሚያስችል የሠራተኛ ሥነ ምግባር መመሪያ (code of conduct guidelines) እና

የጥቅም ግጭት መመሪያ (conflict of interest guidelines) ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም መመሪያዎቹ ስለመዘጋጀታቸው ተጠይቆ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ መሆኑ፤

140. በ2009 ዓ.ም የወጣ በመንግስት ብድር አስተዳደር እና ዋስትና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 46/2009 መሠረት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የውጭ ብድር ጥያቄዎቻቸውን ቅደም ተከተል በማስያዝ፣ የመንግስት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች መሠረት በማድረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረብ የሚኖርባቸው ቢሆንም በዚህ መሠረት ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ማስረጃ ተጠይቆ፤ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤

141. በ2009 ዓ.ም የወጣ በመንግስት ብድር አስተዳደር እና ዋስትና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 46/2009 መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር ምንጮች ብድር ለመውሰድ ከሚያቀርቡት ጥያቄ ጋር የፕሮጀክቱን የአዋጭነት ጥናት እና በብድር የሚወስዱትን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ጥናት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ጥናት አያይዘው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ከ2007 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ያለውን ከውጭ ሀገር ብድር የወሰዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር ምንጮች ብድር ከመውሰዳቸው በፊት ያቀረቡትን የፕሮጀክቶቹን የአዋጭነት ጥናት እና በብድር የሚወስዱትን ገንዘብ መክፈል የሚችሉ ስለመሆናቸው የፋይናንስ አቅም ጥናት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረቡትን ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

142. በ2009 ዓ.ም በወጣው የመንግስት ብድር አስተዳደር እና ዋስትና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 46/2009 መሠረት መንግስት በየዓመቱ ለሁሉም ብድር አይነቶች ከሚቀመጠው አጠቃላይ የብድር ጣሪያ በላይ መበደር የማይቻል መሆኑ እና ጣሪያውም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው የብድር ጫና ትንተና መሠረት መወሰን ያለበት ቢሆንም እ.ኤ.አ በ2012 በአለም ባንክ የሀገሪቱን የንግድ ብድር ጣሪያ (Non Concessional Borrowing Plan Ceiling) የሚያሳይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለበላይ ኃላፊዎች የተጻፈ ደብዳቤ ካልሆነ በስተቀር የብድር ጫና ትንተናን (Debt Sustainability Analysis) መሠረት በማድረግ

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የብድር ጣሪያ ወሰን ማስረጃ ለኦዲቱ ሊቀርብ አልቻለም፤

143. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከውጭ ሀገር የተበደሩትን ዕዳ በውል ስምምነት መሠረት በወቅቱ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ይሁንና በናሙና ተመርጠው ከታዩት መካከል ኢትዮ-ቴሌኮም ከ2016 እ.አ.አ ጀምሮ በየዓመቱ እየተንከባለለ ያለው የውጭ ሀገር ውዝፍ ዕዳ ዋና ገንዘብ 213,992,646.56 ዶላር እና ወለድ 36,208,233.96 ዶላር በጠቅላላ 250,200,880.53 ዶላር፤ የስኳር ኮርፖሬሽን ያልተከፈለ 25,896,154.00 ዶላር እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የዋና ብድር 96,985,963.47 ዶላር ወይም በወቅቱ በነበረ ምንዛሪ መጠን 2,863,112,935.64 ብር በውል ስምምነቱ መሠረት በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ መኖሩ፤

በብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ሪቴንሽን አካውንት አጠቃቀምና ቁጥጥር በተመለከተ

144. የሪቴንሽን አካውንት ተጠቃሚዎች ከዚህ አካውንት የውጭ ምንዛሪ ለመጠቀም ጥያቄ ቀርቦ በንግድ ባንኮች በኩል ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የቀረበው የውጪ ምንዛሬ ጥያቄ ድርጅቶች በቀጥታ ከተሰማሩበት ዘርፍ ጋር ተቀራራቢ ለሆነ ስራ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

145. ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የሪቴንሽን አካውንት መመሪያ መሰረት አንዳንድ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ጥያቄ ቀርቦ በንግድ ባንኮች በኩል ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የቀረበው የውጪ ምንዛሬ ጥያቄ በቀጥታ ከተሰማሩበት ዘርፍ ጋር ተቀራራቢ ለሆነ ስራ መሆኑ በባንኮች ሳይረጋገጥ ወደ ሀገር ውስጥ እቃዎችን የማስመጣት ፈቃድ (ፐርሚት) ተሰጥቷቸው ከሪቴንሽን አካውንታቸው በመጠቀም ከተሰማሩበት ዘርፍ ውጪ ዕቃዎች ያስገቡ መኖራቸው፤ እንዲሁም 15 ባንኮች ከመመሪያው ውጪ ጥሰቱን የፈፀሙ መሆናቸውን ከተከለሱ መረጃዎች በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

146. ብሔራዊ ባንክ የሪቴንሽን አካውንት መጠቀሚያ ፈቃድ በማያድሱ ድርጅቶች ላይ ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ይሁን እንጂ ፍቃዳቸውን

ሳያድሱ የውጪ ምንዛሪ የሚሰበስቡ ሆቴሎች፣ አስጎብኚ ድርጅቶችና ሌሎች ድርጅቶች ፈቃዳቸውን በወቅቱ እንዲያድሱ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ እየሰራ እንዳልሆነ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በኦዲት ወቅት ከታዩ 6 ሆቴሎች እና 2 አስጎብኚ ድርጅቶች ያወጡትን የውጪ ምንዛሪ መሰብሰብ ፈቃድ ሳያድሱ በውጪ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ እየተቀበሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡

147. ብሔራዊ ባንክ በህገወጥ መልኩ የሪቴንሽን አካውንት የሚጠቀሙትን አካላት ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ እቅድ በማዘጋጀት በየጊዜው አፈጻጸሙን ሊከታተልና ሊገመግም ይገባል፡፡

148. ይሁን እንጂ ብሔራዊ ባንክ በህገወጥ መልኩ የውጪ ምንዛሪ የሪቴንሽን አካውንት ግብይት የሚሰሩትን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የጋራ እቅድ የማያቅድ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተደረጉት የክዋኔ ኦዲቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

149. በአጠቃላይ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ላይ በተከናወኑት የክዋኔ ኦዲቶች የተገኙ የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት የተቋቋመለትን ዓላማ በኢኮኖሚያዊና በውጤታማነት ለማሳካት ዝርዝር መርሃ ግብር አዘጋጅቶ በተሰጡት የማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ ሊወስዱ የሚገባ ከመሆኑም በላይ በየደረጃው የሚገኙ ተቆጣጣሪ አካላትም ተገቢውን ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የልዩ ኦዲት ስራዎች

150. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት ከተጠየቁት የልዩ ኦዲት ስራዎች መካከል 7 ኦዲቶች ሥራቸው ተጠናቀው ሪፖርቱ ለጠያቂ አካል የተላኩ ሲሆን፤ 5 ሌሎች ልዩ ኦዲቶች ደግሞ በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

151. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው የሚታወቅ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እርምጃ ስለመውሰዳቸው እያሳወቁ አለመሆኑ፤

152. በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት በ2011 በጀት ዓመት ኦዲትን አስመልክቶ በ68 መ/ቤቶች እና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ግኝቶች ላይ ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት የተሰጠበት ብር 1,787,421,015.63 ውስጥ ተመላሽ የተደረገ ብር 261,823,793.04 ብቻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ አፈጻጸም ተመላሽ ሊደረግ ከሚገበው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በመቶኛ 14.64% ብቻ ሲሆን፤ ቀሪው ብር 1,525,597,222.59 ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ እና በገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶችም ብር 3,680,883.74 ያለመመሪያና ያለ በቂ ማስረጃ የተፈጸመው ክፍያ ላይ እርምጃ ሳይወሰድበት የቀየ መሆኑ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልተወሰደበትና ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

153. በተጨማሪም በገቢ አሰባበሰብ ዙሪያ እስከ 2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በቀሪነት የሚታይ፤ በ5 የገቢዎች እና በ6 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,083,889,988.63 መኖሩና በ68 ግብር ከፋዮችም ላይ እርምጃ እንዳልተወሰደ ታውቋል፡፡

154. ስለዚህ የተከበረው ምክር ቤት በተሰጠቸው የኦዲት ማሻሻያ ሀሰብ መሰረት ማስተካከያ ያለደረጉ እና የመንግስት ገንዘብ እንዲመለስ ባላደረጉ መ/ቤቶች ላይ አስፈለጊው እርምጃ እንዲወሰድ በትኩረት መታተል ያስፈልጋል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

155. የለውጥ ሥራዎችን በተመለከተ የዓመቱ ዕቅድ ማጠንጠኛ የነበረው ባለፉት የበጀት ዓመታት ተጀምረው የነበሩትን ሥራዎች አጠናክሮ ማስኬድ ነበር፡፡ በተለይ እስከ አሁን ትልቅ ችግር የነበረውና አሁንም ያልተፈታው የውጤት ተኮር ምዘናውን ሥርዓት ኦቶሜት የማድረጉ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን ቸግር ለመፍታት ቀደም ሲል በትምህርት ሚኒስቴር አሁን በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ድጋፍ የተወሰነ ርቀት ቢኬድም በተለያዩ ምክንያቶች ችግሩ በዚህ ዓመትም ሊፈታ አልቻለም፡፡ ነገር ግን በሚኒሰቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ ድጋፍ ጉዳዩ መልክ ይዞ የነበረ ቢሆንም የሶፍትዌር ባለቤትነት እንደገና ወደ ትምህርት ሚኒስቴር በመመለሱ ንግግሩን እንድንጀምር አስገድዶናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከትምህርት ሚኒስትሩ ጋር ውይይት ተደርጎ ሶፍትዌሩን ወስደን ለመጠቀም እየተሠራ ይገኛል፡፡

156. በሌላ በኩል ከተቋም እስከ ፈጻሚ ያለው ዓመታዊ፣ የሩብ ዓመት፣ ወርሃዊ እና ሳምንታዊ ዕቅዶችን በሚገባ በማናበብ አፈጻጸምን በማስረጃ በማስደገፍ የመመዝገብ፣ ምዘናም ሲደረግ እነኚህ ተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ በመመስረት ሠራተኛውንም ሆነ ተግባራትን ከመመዘን ረገድ ባለፉት ዓመታት የነበሩ ውስንነቶች አሁንም የሚታዩ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መሻሻል ይታያል፡፡ እነኚህን ውስንነቶች ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ የኦቶሜሽን ሥራ የማፋጠንና የግንዘቤ ማዳበሪያ ተግባራት አሁንም ትኩረት አድርገን በቀጣይ የምንሠራባቸው ናቸው፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

157. እንዳለፉት ዓመታት ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና በተለይ በፋይናንስና ህጋዊነት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቶች ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት እንዲሁም የአካባቢ ጉዳዮች በዕቅድ ውስጥ ቋሚ የሆነ የዕቅድ ዝግጅት አቅጣጫ ተቀምጦ በዚሁ መሠረት የዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት እየተፈጸመ ይገኛል፡፡

158. በሌላ በኩል እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በዚህም ዓመት ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት እንደዚሁም የኤ. አይ. ቪ. ኤዲስ ቀናት በተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ታጅበው የCOVID-19 ፕሮቶኮልን ባገናዘበ ሁኔታ በመ/ቤቱ ተከብሯል፡፡ በተጨማሪም በየሁለት ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ በCOVID-19 ምክንያት በዕቅዱ መሠረት ባይካሄድም የፎረሙ የአመራር ኮሚቴ ስራውን በማስቀጠል ላይ ናቸው፡፡

159. ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ለማድረግ የነፃ ትምህርት ዕድል በማፈላለግ በተደረገው ጥረት በዚህም ዓመት 7 ለሚሆኑ ተጨማሪ ሴት ሠራተኞች ዕድሉ የተመቻቸ ሲሆን ሰባቱም ሠራተኞች ዕድሉን ተጠቅመው በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ቀደም የትምህርት እድሉን ካገኙት መካከል 4 ሴቶች በዲፕሎማ፣ 4 ሴቶች በዲግሪ ትምህርታቸውን የጨረሱ ሲሆን፣ 1 ወንድ እና 1 ሴት በአሽከርካሪነት ሙያ፣ 1 ሴት በምግብ ዝግጅት ሙያ ተመርቀዋል፡፡

160. የአካባቢ ጉዳዮችን በተመለከተ እየተተገበረ ያለው የወረቀት አልባ ሥርዓቱ ተጠናክሮ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በሌላም በኩል በተለያዩ የአካባቢና የዘላቂ ልማት ግቦች በኦዲት አርዕስት ተይዘው በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

161. በሌላ በኩል የመንግሥትን ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በመ/ቤታችን የህፃናት ማቆያ የማደራጀት ሥራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ ለሕፃናት ማቆያ ለሚያስፈልጉ

ሠራተኞች መዋቅሩ ቢፀድቅም፤ ደመወዝ ባለመፈቀዱ ሥራ ማስጀመር አልተቻለም፡፡ በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የደመወዝ ስኬል ጥናት ለተከበረው ም/ቤት ቀርቦ ባለመፅደቁ ይኸው የደመወዝ ስኬል ጥያቄ ሲወሰን በፍጥነት የሠራተኛ ቅጥር በማከናወን የህፃናት ማቆያውን ሥራ የምናስጀምር ይሆናል፡፡

<u>የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ</u>

162. እንደሚታወቀው የመ/ቤታችን የማሠልጠኛ ማዕከል ቀሪ ተግባራት በሙሉ ተጠናቅቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ በዚሁ ማዕከል ሠራተኞቻችንን በመጠቀም የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች መስጠት የተጀመረ ቢሆንም፤ ቋሚ አሰልጠኞችን ለመቅጥር በተከበረው ም/ቤት መዋቅሩ የፀደቀ ቢሆንም ለቦታው ደመወዝ ባለመፈቀዱ ምክንያት ቋሚ አሰልጣኞችን ቀጥሮ የሥልጠና ማዕከሉ በሙሉ አቅሙ እንዲሠራ ማድረግ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በየካቲትና መጋቢት/2012 የተወሰነ ሥልጠና እንደተሰጠ የCOVID-19 ወራርሽኝ በመከሰቱ ለዓመቱ የተያዘውን የሥልጠና ዕቅድ እንደታሰበው ማስቀጠል አልተቻለም፡፡

163. ካለይ የተጠቀሱት እንቅፋቶች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ11 ኦዲተሮችና ለ20 የድጋፍ ዘርፍ በድምሩ 31 ለሚሆኑ ሠራተኞቻችን የአቅም ማጎልባቻ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡

164. በሌላ በኩል ከውጭ ሀገር በሚገኙ የሥልጠና ዕድሎችም በመጠቀም በተለይ የኦዲተሮቻችንን አቅም ለማጎልበት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት በኮቪድ 19 ምክንያት የውጭ አገር ሥልጠና በአካል ባይሰጥም ኦዲተሮችና የሥራ ኃላፊዎች የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በቨርቹዋል (Zoom) ባዘጋጁት መድረክ እንዲሰተፉ ተደርጓል፡፡

165. ቀደም ሲል የተጠናቀቁ የዳታ ማዕከል ግንባታ፤ የሰርቪላንስ ሲሰተም፤ የኔትወርክና ተጓዳኝ ሥራዎች እንዲሁም የIP ቴሌፎን ሲስተሞችን በመጠቀም በዚህም ዓመት የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱንና ቅልጥፍናው ይበልጥ ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዓመት በUNDP ድጋፍ የዳታ ማዕከሉን የመቆጣጠሪያ መሳሪያ የማስፋት፤ የአምስቱንም የሥልጠና ክፍሎች ወደ ስማርት ቴክኖሎጂ

የመቀየር፣ የመ/ቤቱን አዳራሾች የመገናኛ ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም በWorld Bank ድጋፍ የተጨማሪ የመስክና የአውቶሞቢል ተሽከርካሪ ግዢ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡

166. ከጥር 2008 እስከ 2013 ስንሰራበት የነበረው የመ/ቤታችን ስትራቴጂክ ዕቅድ በመጠናቀቁ ከ 2013 እስከ 2018 የሚተገበር ሀገራዊ ሁኔታን እና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን በማገናዘብ፣ እንዲሁም የጸደቀውን የመ/ቤቱን ማዋቅር ያገናዘበ ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

167. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 645 እና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 359 እና 5 የበላይ አመራር በድምሩ 1013 የሰው ሀይል ነው፡፡ በየካቲት 30/2012 በመ/ቤቱ ሥራ ሲታቀድ የነበረው የሰው ሀይል መረጃ በኦዲት ዘርፍ 444፣ በድጋፍ ዘርፍ 208 በድምሩ 652 የነበሩ፡፡ በዓመቱ 50 ኦዲተሮች እና 11 ለድጋፍ ዘርፍ በድምሩ 61 ሰራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ ከኦዲት 20 ከድጋፍ ዘርፍ 16 በገዛ ፍቃዳቸው፣ 2 በጡረታ እና 1 ሰራተኛ የኮንትራት ጊዜው በመጠናቀቁ በድምሩ 36 ሰራተኞች ከመ/ቤቱ ለቀዋል፡፡

168. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 462 የኦዲት ባለሙያዎች (308 ወንዶችና 154 ሴቶች)፣ 198 የድጋፍ ሰጪ (83 ወንዶችና 115 ሴቶች) ሠራተኞች በአጠቃላይ 660 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ 353 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም፣ መዋቅር ብቻ ጸድቆ ደመወዙ ስላልተፈቀደ፣ በተለይም አዳዲስ በተፈቀዱት የስራ መደቦች ለመቅጠርም ሆነ መድቦ ለማሰራት አስቸጋሪ በመሆኑ እና ባለው የሠራተኛ ፍልሰት ምክንያት ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

የኮቪድ-19 ወራርሽኝ መከላከል ፕሮቶኮል

169. በዓለማችን የተከሰተውን የኮሮና ወረርሽኝ ለመከለከል እንዲሁም የሠራተኛውን ጤና ከመጠበቅ አንጻር የኮሮና መከላከል ፕሮቶኮል በማዘጋጀት የኦዲት ስራዉ የተጀመረ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረትም የኮቪድ-19 መከላከያ የሚሆን የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፣ የእጅ ማጽጃ ሳኒታይዘር በተቀመጠዉ ስታንዳርድ መሰረት ለሰራተኛዉ በየወሩ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከሳይንስና ኢኖቬሽን ሚ/ር ከእጅ ንክኪ ነጻ የሆነ የሳኒታይዘር

መጠቀሚያ ለመ/ቤታችን በስጦታ የተበረከተልንን በቢሮ መግቢያ እና መዉጫ ላይ በማስቀመጥ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤቱን ህንጻ ሙሉ በሙሉ የማፅደት (የማስረጨት) ሥራ ተከናውኗል፡፡ ከህብረተሰብ ጤና ኢንስቲዩት ጋር በመነጋገር ለ99 የመ/ቤቱ ሰራተኞችም በፍላጎትላይ የተመሰረተ የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ተደርጓል፡፡ የተወሰኑ ሰራተኞችም ቫይረሱ የተገኘባቸዉ አገግመው ወደስራቸው የተመለሱ ሲሆን፤አንድ የኦዲት ዳይሬክተር ግን በዚሁ በሽታ ሕይወታቸው አልፏል፡፡

የ2012 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

170. በ2012 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 93,789,937.00 የተፈቀደ ሲሆን፤ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዓመቱ ሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 78,169,361.73 ወይም የዕቅዱ 83.04% ነው፡፡ በአዋጃችን መሰረት ስራ ላይ የዋለው ሂሳብ ምክር ቤቱ በሰየማቸው ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለም/ቤቱ ቀርቧል፡፡

2013 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

171. በ2013 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 95,340,930.00 ተፈቅዷል፡፡ ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ለመጠቀም ታቅዶ የነበረው ብር 77,415,734.00 ሲሆን ሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 64,600,795.18 ወይም የዕቅዱ 83.04% ነው፡፡ የተቀረው በጀት ብር 30,740,134.82 ወይም 32.24% በቀሪ ወራት ውስጥ ለማከናወን ለታቀዱት ተግባራት በዕቅዱ መሠረት ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮና የተወሰዱ እርምጃዎች

172. በዚህ ዓመት ካጋጠሙን ችግሮች ሁሉ የከፋው የCOVID-19 ወራረሽን ያስከተለው ችግር ነው፡፡ ወረርሽኙ በመከሰቱና አብዛኛው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ከቤት ሆነው እንዲሠሩ በመደረጉና በዚህም ምክንያት የኦዲት ሥራው እስከ መስከረም የመጨረሻው ሳምንት በመቋረጡ ዕቅዳችንን እንድንከልስ አስገድዷል፡፡ በዚህም ምክንያት የባለበጀት መ/ቤቶችን እንደቀደሙት ዓመታት 100% ኦዲት ማድረግ አላስቻለንም፡፡ ከመስከረም በኋላም ቢሆን የባርካታ ኦዲት አስደራጊ መ/ቤቶች

ሠራተኞች በወራርሽኙ መጠቃት ምክንያት የኦዲት ሥራው እንዲጓተት፤ የመውጫ ስብሰባ በወቅቱ እንዳይደረግና በአጠቃላይ ኦዲቱ በተከለሰውም ጊዜ እንዳይጠናቀቅ አድርጓል፡፡

173. ሌላው እስከ አሁን ያልተለመደውና በዚህ ዓመት ያጋጠመን ችግር የተወሰኑ መ/ቤት ሀላፊዎች ሰበብ አስባብ በማቅረብ ኦዲት ላለመደረግ ያደረጉት በፍፁም ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ነው፡፡ የተከበረው ም/ቤት ይህንን ተገንዝቦ አፋጣኝ እርምጃ ከወዲሁ ሊወስድ ይገባል፡፡

174. በተመሳሳይ ሁኔታ እስከ አሁን ባልተለመደ መንገድ የተወሰኑ ክልሎች በተለይ ዋና ዋናዎቹ ኦዲት ልታደርጉ አትችሉም፤ ከየክልሎቹ ካልተፈቀደላችሁ አንተባበርም የሚሉ ዝንባሌዎች በርክት ብለው ታይተዋል፡፡ ይህ ጉዳይ በፍጥነት ካልታረመ ጉዳቱ ከፍተኛ በመሆኑ የተከበረው ም/ቤት ከሁሉም ክልሎችና ከፌዴራል መንግሥት መሪዎች ጋር በመነጋገር ለጉዳዩ እልባት ሊሰጥ ይገባል፡፡

175. ባለፉት ዓመታት እንደነበረው ሁሉ አሁንም ያልተሻሻሉትና በዚህም ዓመት የቀጠሉት ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ በኦዲተሮቻችን የሚጠየቁትን ማስረጃዎች በወቅቱ ያለማቅረብ ወይም ያለመስጠት፣ ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት፤ የመውጫ ስብሰባ በወቅቱ አለማድረግ እና የመውጫ ስብሰባውም ከተደረገና ለኦዲተሮች ሌላ ስምሪት ከተሰጠ በኋላ በኦዲት ወቅት ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡትን ማስረጃዎች አሉን በማለት በርካታ ሠነዶችን መ/ቤታችን ድረስ ማምጣት፣ ለረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት ናቸው፡፡ እነኚህ ችግሮች እንዲቀረፉ ባለፉት ዓመታት ጥረቶች ቢደረጉም፤ የተወሰደ እርምጃ በቂ ባለመሆኑ፤ የሚፈለገውን ውጤት እያሳዩ አይደለም፡፡ አሁንም ቢሆን እነኚህን ችግሮች ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በአፋጣኝ እንዲያስወግዱና ለኦዲቱ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ አጥብቀን እየጠየቅን፤ ገንዘብ ሚኒስቴርና ጠቅላይ ዐቃቢ ህግም አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ እናሳስባለን፡፡

176. ሌላው ባለፈው ዓመት እንደነበረው ሁሉ በዚህም ዓመት ሥራችንን በወቅቱ እንዳናከናውን ፈታኝ ያደረገው ጉዳይ በተለያዩ አካባቢዎች የነበረው የፀጥታ መደፍረስ

ጉዳይ ነው፡፡ የተለያየ መንገድ በመጠቀም የፀጥታው ችግር ኦዲታችንን ወደ ማቋረጥ እንዳያደረሰን ወቅታዊ እርምጃ በመውሰድ ኦዲተሮችን አንፃራዊ ሠላም ወደአለበት አካባቢ በማዘዋዋር ዕቅዳችንን ለመፈፀም ከፍተኛ ጥረት በመደረጉ ችግሩ በዕቅድ ክንውን አፈፃፀማችንን ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፀዕኖ እንዳያስከትል ለማድረግ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ኦዲተሮቻችን በችግሩም ውስጥ ሆነው ሥራቸውን ለማጠናቀቅ ባደረጉት ጥረት ካጋጠመን ችግር አንፃር ጥሩ የሚባል አፈፃፀም ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆናው ሀላፊነታቸውን የተወጡትን ሰራተኞች በም/ቤቱ ፊት ላመሰግናቸው እወደለሁ፡፡

የ2013/14 ኦዲት ዓመት ዕቅድ

177. በ2013 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 186 የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 8 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 178 መ/ቤቶችና 52 ቅርንጫፎቻቸው እና 3 የማጠቃለያ ሂሳቦች በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም ከመጋቢት 2013 እስከ ጥር 2014 ድረስ ባለው ጊዜ 24 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክትትል ኦዲቶችን በማከናወን 30 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በ295 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እና 23 የማረጋገጥ ስራዎች(Verifications); እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡ በሌላም በኩል የ2013 የመንግስት የተጠቃለለ ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ፣ እንዲሁም የተጀመሩትን ልዩ ኦዲት ስራዎች በማጠናቀቅ፣ በተጨማሪም ከአቃቢ ሕግና በፌዴራል ፖሊስ የተጠየቁትን የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች አቅም በፈቀደ መጠን ለማጠናቀቅ ታስቧል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

178. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የእርዳታ ሂሳቦችን

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

179. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2012 በተከናወኑና ለመ/ቤታችን የደረሱ ኦዲቶች ላይ የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

የመንግስት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት ክትትል

180. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና መጋቢት/2012 እስከ ሚያዝያ 30/2013 ዓ.ም ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 26 (ሁለት ድርጅቶች ከስራቸው የሚተዳደሩ 6 ተቋማት ጭምር 32) ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 129 በድምሩ 155 (ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡

181. ለመ/ቤታችን የደረሱት የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ሲተነተኑ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 105፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 39፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 5፣ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 6 በድምሩ 155 ናቸው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

182. ኮርፖሬሽኑ በ2012 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 46,774,950.00 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 44,984,049.00 ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ብር 32,636,894.00 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 30,458,813.00 ወጪ ያደረገ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ብር 271,026.00 የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ውዝፍ የኦዲት ሥራ ያላቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች

183. መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ሂሣባቸውን ዘግተው በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉና ከአንድ ዓመት በላይ ውዝፍ የኦዲት ሥራ ያለባቸው 44 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆን፣ ኦዲቱ ወደ ኋላ የቀረበትን መንስኤ አውቆ ተገቢውን እርምጃ ለመውሳድ በተሞከረበት ወቅት፣ አንዳንዶቹ ድርጅቶች የባለሙያ እጥረት እንዳለበቸው፣ሌሎች ደግሞ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ለመከተል ያላቸውን ዝግጅትና የሂሳብ አሰራር ለውጥ ጋር ያጋጠማቸውን ችግሮች ያነሱ ሲሆን፣ በአንዳንድ ድርጅቶች ከዋና ኦዲተር መ/ቤት ዕውቅና ውጪ ሂሳባቸውን ኦዲት ለማስደረግ አዝማሚያ መኖሩ እና አሁን ደግሞ የኮቪድ መከሰት እንደምክንያት እየቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ፣ የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት በቂ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።

ማጠቃለያ

184. በተከለሰው ዕቅድ መሠረት በ118 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እና 36 ቅርንጫፎች ላይ ኦዲት ለማከናወን ታቅዶ በ117 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እና 35 ቅርንጫፎች ላይ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ ቀሪው አንዱ መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 783/2005 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ሲሆን፣ በጀት በቀጥታ ስለማይመደብለትና በማቋቋሚያ አዋጁም መሠረት የአካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በጠቅላላ ጉባኤ በሚሰየም የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል የሚል በመሆኑ ኦዲት ስላልተደረገ የዕቅድ ክንውኑን ወደ 99.15% ዝቅ አድርጎታል፡፡

185. በሌላ በኩል የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 23 አዳዲስና 4 የክትትል ኦዲት በድምሩ 27 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 17 አዳዲስና 3 የክትትል በድምሩ 20 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል የ5 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በመ/ቤታችን በኩል ተጠናቅቆ ረቂቅ ሪፖርቶቹ ለመ/ቤቶቹ የተላኩ ቢሆንም ኦዲት ተደራጊዎች የተለያየ ምክንያት በማቅረብ የመውጫ ስብሰባ ባለመደረጉ የመጨረሻው ሪፖርት ሊጊዜው ወጪ ማድረግ አልተቻለም። ቀሪው አንድ ኦዲት ሥራው የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የደረሰ ቢሆንም፤ የኦዲት ስራው ባለመጠናቀቁ ወደ 2013/14 የኦዲት ዓመት ተሻግሯል፡፡

186. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ196 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት ለማከናወን ታቅዶ 197 ኦዲቶች (አንድ ልዩ ኦዲት ጨምሮ) ወይም የዕቅዱ 100% ኦዲቶች ተከናውኗል፡፡

187. የኦዲት ግኝት እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ የተወሰኑ ጥረት የሚያደርጉ መ/ቤቶች ቢኖሩም በአጠቃላይ ሲታይ እስከ አሁን በመ/ቤታችን ሲሰጡ የነበሩ የማሻሻያ አስተያየቶችን በመተግበርና በመንግሥት የተዘረጋውን የፋይናንስ፤ የግዢ እና የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም እንደዚሁም ሌሎች የመንግሥት አሰራሮችንና ሥርዓቶችን በመከተል ባለፉት ዓመታት የታዩትን የአሠራር ግድፈቶችን ያረሙ መ/ቤቶች የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ለዚህ ደግሞ መንስኤው በየዓመቱ የሚታዩ ግድፈቶችንና ጥፋቶችን በተመለከተ በየደረጃው የተጠያቂነት እርምጃ ተወስዶ ሀላፊዎችና ሠራተኞች ሊወስዱ የሚገባውን ትምህርት አለመውሰዳቸውና ተጠያቂ እንደሚሆኑ ባለማሰባቸው እንዲሁም በተጨባጭም የሚያዩት ነገር ባለመኖሩ ነው፡፡

188. የገንዘብ መጠን የመጨመርና የመቀነስ ጉዳይ ካልሆነ በቀር እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ በ2012 በጀት አመትም ዋንኞቹ የኦዲት ግኝት ሆነው የቀጠሉት ከጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ የውዝፍ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ ወይም አለመወራረድ፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚከናወኑ ግዥዎችና እንደዚሁም ከህግና ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ አላግባብ የሚፈጸሙ የጥቅማ ጥቅምና ሌሎች ክፍያዎች፣ አላግባብ በብልጫ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤ ከውል አስተዳደር

ጋር የሚታዩ ግድፈቶች፤ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ እንዲሁም ውዝፍ ገቢ አሰበሰብ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ተደጋጋሚ ግድፈቶች፣ ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ጉድለቶች፣ የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም ጋር ተያየዘው የሚታዩ ክፍተቶች፤ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረጉት የክዋኔ ኦዲቶች በርካታ ሊዘረጉ ሲገባ ያልተዘረጉ የአሠራር ሥርኣቶች የየመ/ቤቶቹን ቅልጥፍናና ውጤታማነት እንዲሁም ለተፅልኮ ስኬት አስተዋፅኦ ያደርጉ የነበሩ የህግ እና የአሠራር ሥርዓቶች እንደዚሁም ተዘርግቶ የማይተገበሩ አሠራሮችና ሥርዓቶች፤ በመ/ቤት ውስጥም ሆነ ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለው የቅንጅትና ትብብር ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ግድፈቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

189. ስለሆነም የህዝብና የመንግስት ጥቅም እንዲጠበቅ ከተፈለገ እነኚህ የኦዲት ግኝቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው እርምጃ ተወስዶ ሊስተካከሉና ሊታረሙ ይገባል፡፡ ይህንን የማያደርጉ ተቋማት ሀላፊዎችና ሠራተኞች ደግሞ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተጠያቂ መደረግ ይገባል፡፡

190. በመሆኑም የተከበረው ም/ቤት የተሠጣቸውን የመንግሥትና የህዝብ አደራ ያልተወጡ የመንግሥት መ/ቤቶች የሥራ ሀላፊዎችና ሠራተኞች ላይ ተገቢው የተጠያቂነት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ የሚወሰደው እርምጃ የአንድና ሁለት ዓመት የኦዲት ግኝት ብቻ ሳይሆን ባለፉት ዓመታት የተገኙት እስካሁን ያልተስተካከሉትን የፋይናንስና ህጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲት እንዲሁም የልዩ ኦዲት ግኝቶችን ሊያካትት ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ጠንካራና ጥብቅ እርምጃ ካልተወሰደ የህዝብና የመንግሥት ገንዘብ እንደባከነ እንዲቀር የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ተገቢውን የአሠራርና ሥርዓት ባለመዘርጋትና ባለመፈጸም በዜጎች ላይ ሲደርስ የነበረውን ደካማ የአገልግሎት አሰጣጥ ጉድለት ማረም አያስችልም፡፡ በመሆኑም የተከበረው ም/ቤት፤ የሚኒስትሮች ም/ቤት፤ የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲሁም መ/ቤቶቹ ተጠሪ የሆኑባቸው ተቋማትና የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አሁንም አግባብ የሆነውን ጥብቅ የተጠያቂነት እርምጃ እንዲወስዱ እያሳሰብኩ በጥሞና ስላደመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አባሪ - 1

በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እና ባለፉት ተከታታይ ሁለት ኦዲቶች

ሀ/	ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው	X
ለ/	አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	XX
ሐ/	ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሂሣባቸው አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) የተሰጣቸው	E

ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት ሂሳብ		
X	XX		2010	2011	2012
		የፋይናንስና ኮሚዩኒኬሽን መ/ቤቶች			
	1	የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት	XX	X	XX
	2	ቱሪዝም ኢትዮጵያ	E		XX
	3	የኢትዮጲያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	E	X	XX
	4	ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን	XX	X	XX
	5	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	X		XX
1		የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	E	E	X
2		የፋይናስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	E	E	X
3		ማዕከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ	XX	E	X
4		ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	X	X	X
5		ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	X	X	X
6		የወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	E	X	X
7		ብሄራዊ ቴአትር	E	E	X
8		ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር	E	E	X
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች			
	6	የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል			XX
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
	7	የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	XX	X	XX
	8	የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች			
9		የግብርና ሚኒስቴር	X	X	X
10		የተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን			X

ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት ሂሳብ		
X	XX		2010	2011	2012
11		የአዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የፕሮጀክት ሂሳብ		X	X
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
12		የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
13		ኦዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ	X	XX	X
14		ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	X	XX	X
15		አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
16		የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
17		የኢትዮጵያ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኢንስትቲዩት	X	X	X
18		የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት	X	E	X
19		የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	X	E	X
20		የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	X	XX	X
21		የወልድያ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
22		የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
23		የወራቤ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
24		የመቱ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
25		ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ኤጀንሲ	E	X	X
26		የፌ/የቴክ/ሙ.ያ ት/ሥ/ ኤጀንሲ	X	X	X
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች			
27		የኢሚግሬሽን ዜግነትና ወሳኝ ኩነት			X
28		ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	E	X	X
29		የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ			X
		ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት			X
30		አርሲ ዩኒቨርሲቲ	E	E	X
31		ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
32		ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
33		ሃረማያ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
34		ጅማ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
35		ጂንካ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
36		ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
37		ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
38		ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
39		ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
40		አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
41		ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	X	X	X

አባሪ - 2

ሂሣባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች

(ከአንድ እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት የዘገዩ- እስከ ሚያዝያ/2013)

ተ.ቁ	የልማት ድርጅቱ ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት	ወደኃላ የቀረበት በ...ዓመት
1	ስኳር ኮርፖሬሽን(በስሩ ከሚገኙ የስኳር ፋብሪካዎች ጭምር)	30 ጁን 2013	7
2	ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር	7-Jul-14	6
3	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት	7-Jul-16	4
4	የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2008	4
5	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት	ሰኔ 30/2008	4
6	የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን	ሰኔ 30/2008	4
7	ኢትዮ-ቴሌኮም	30-Jun-17	3
8	የኢትዮጵያ ማዕድን ፣ነዳጅና ባዮፌዉል ኮርፖሬሽን	ጁን 30/2017	3
9	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ	ሰኔ 30/2009	3
10	የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት	ሰኔ 30/2009	3
11	የግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ሰኔ 30/2009	3
12	የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን	ሰኔ 30/2009	3
13	የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን- በስሩ ከሚተዳደሩ ኢንዱስትሪዎች ጋር	ሰኔ 30/2009	3
14	የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት	ሰኔ 30/2009	3
15	የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲተዩት/ገነት ሆቴል/	30 ጁን 2017	3
16	የሆቴል ልማት ኢ.ማ(ኢ.ኢ. ሒልተን)	30 ጁን 2017	3
17	የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	3
18	የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ	ሰኔ 30/2009	3
19	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2009	3
20	የመንግስት ሰራተኞ ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ሰኔ 30/2009	3
21	ሸበሌ ትራንስፖርት ኢ.ማ	ሰኔ 30/2009	3
22	የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት	7-Jul-17	3
23	የመንግስት ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት	ጁን 30 /2018	2

ተ.ቁ	የልማት ድርጅቱ ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት	ወደኃላ የቀረበት በ...ዓመት
24	የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2010	2
25	የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ድርጅት	ጁን 30/2018	2
26	የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት	ሰኔ 30 /2010	2
27	የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ.ማ	ሰኔ 30 /2010	2
28	የኢትዮ-ጂቡቲ ስተንደርድ-ጌጅ ባቡር አ.ማ	ዲሰ. 31/2018	2
29	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	30-Jun-19	2
30	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን	30-Jun-18	2
31	ኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30 /2010	2
32	የመከላከያ ኮንስትራክሽን ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	2
33	የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30 /2010	2
34	የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30 /2010	2
35	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ	ጁን 30 /2018	2
36	የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት	ሰኔ 30 /2011	1
37	ብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት	7 ጁላይ 2019	1
38	ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት	ሰኔ 30/2011	1
39	የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን	30-Jun-19	1
40	የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት	ሰኔ 30 /2010	1
41	የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2011	1
42	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	30 ጁን 2019	1
43	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ሰኔ 30 /2011	1
44	የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት	ጁን 30 /2019	1

አባሪ-3

ልዩ ኦዲት የተካሄደባቸው አርዕስቶች

1.	የኢትዮጵያ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የጃፓን አለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ የማስፋፊያ ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ሂሣብ ኦዲት
2.	ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲየ2011 በጀት ዓመት የስቴፕለር ግዥ ሂሳብ
3.	የኢፌ.ዲ.ሪ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የአዳማ እርሻ መሣሪያዎች ኢንዱስትሪ የመስኖ ኘሮጀክት ግንባታ ልዩ ኦዲት
4.	የኢፌ.ዲ.ሪ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የሃይቴክ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ስማርት ኢነርጂ ሜትር ግዥ ልዩ ኦዲት
5.	የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፓሬሽን የአዳዲስ ፋብሪካዎች ግንባታ ልዩ ኦዲት
6.	የኢትዩድያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት የነዳጅ የዱቤ ሽያጭ ልዩ ኦዲት
7.	የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ የመድኃኒት ግዥ ልዩ ኦዲት